# ምልክት

... የቃሉን መነበብ። ለጉባኤው መዝጊያ፡ እንድትቆሙ የምጠይቃችሁ ምክንያት... **ዘ-ስታር ስፓንግልድ ባነር** ሲጫወቱ፡ ትቆማላችሁ። አይደል? [ጉባኤው “አዎን፡” አለ።—አርታዒ።] ታዲያ ለእግዚአብሔር ቃል ለምን አንቆምም? ክብር ነው። እንግዲህ በዘፀአት መጽሐፍ፡ 12ኛው ምዕራፍ፡ ከ12ኛው ቁጥር ጀምሮ፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል 12ኛ እና 13ኛ ቁጥር፡ ማንበብ እፈልጋለሁ።

> **በዚች ሌሊት በግብፅ አገር አልፋለሁ፥ በግብፅም—አገር ከሰው እስከ እንስሳ ድረስ... በኵርን ሁሉ እገድላለሁ፡ በግብፅም አማልክት ሁሉ... ላይ፡ እፈርድባቸዋለሁ፥ እኔ እግዚአብሔር ነኝ።**
>
> **ደሙም ባላችሁበት** ቤቶች **ምልክት ይሆን**ላችኋል፥ **ደሙንም ባየሁ ጊዜ፡ ከእናንተ እልፋለሁ፡ እኔም የግብፅን አገር በመታሁ ጊዜ፡ መቅሰፍቱ ለጥፋት አይመጣባችሁም።**

2 ርዕሴ፥ **ምልክት** ነው።

3 አንገታችንን ዝቅ እናድርግ። እናም በዚህ በተቀደሰ ጊዜው፡ ወደ እርሱ በጸሎት ከመቅረባችን በፊት፡ ዛሬ ከሰአት በኋላ እግዚአብሔር እንዲመልስላችሁ የምትፈልጉት ልመና አላችሁ? ካላችሁ እጆቻችን ከፍ አድርጉና፡ ሊያደርግላችሁ የምትፈልጉትን ነገር በልባችሁ አስቡ። በህንጻው ውስጥ ያላችሁ ሁላችሁ፡ ሊያደርግላችሁ የምትፈልጉትን ነገር አስቡ።

4 የሰማይ አባታችን ሆይ፡ አንተ የማትለወጥ አምላክ ነህ፡ ስለዚህ እርስ በርሳችን እጆቻችን ተያይዘን ሳለን፡ ዛሬ ከሰዓት በኋላ፡ ጸ—ጸሎታችንን ትመልስልን ዘንድ እንጸልያለን። እጆቼም ወደ ላይ መሆናቸውን አስብ። ማለትም፡ ጌታ ሆይ፡ ዛሬ እዚህ ያለውን ሰው ሁሉ እንድትፈውስ፡ ልመናዬን፡ በይፋ አሳውቃለሁ፡ የጠፋውን ሁሉ አድን። አንተ ራስህ፡ “አብን በስሜ፡ ማንኛውንም ነገር ብትጠይቁ፡ እኔ አደርገዋለሁ፡” ብለኸናልና። አሁንም፡ ጌታ ሆይ፡ እንደ አንድ መንጋ ህዝብ፡ እንደሚያምኑ ልጆች ተባብረን እናምናለንና በአንድነት እርዳን። ጌታ ሆይ፡ በቃልህ ተናገር። ቃልህ እውነት ነው። ልባችንን ይባርክ።

5 ስለዚህ ስብሰባ እናመሰግንሃለን። ስለ ወንድም ግራንት፡ እና ስለ ስራተኞቹ ሁሉ፡ እና ስለ ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት እና ሰዎች እናመሰግንሃለን። ስላደረግህልን ነገር ሁሉ፡ ጌታ ሆይ፡ እናመሰግንሃለን። አባት ሆይ፡ ብዙዎቻችን በሌላኛው አድማስ እስክንገናኝ ድረስ፡ በድጋሚ የማንተያይ እዚህ ብዙዎች ልንኖር እንችላለን። በዚህ ምድር ላይ አብረን የምንቀመጥበት የመጨረሻው አገልግሎት ይህ ሊሆን ይችላል። መንፈስ ቅዱስ መጥቶ በአንድነት ይባርከን፡ ፍላጎታችንን ያገልግል። በኢየሱስ ስም እንጸልያለን። ኣሜን።

አረፍ በሉ።

6 እነሰ ያለች ማስታወሻ ይዣለሁ፡ አንዳንድ ቅዱሳት መጻሕፍትን እና ጥቃቅን ነገሮችን ጽፌባታለሁ። በፊት በአእምሮዬ ማስታወስ እችል ነበር፡ አሁን ግን፡ ታውቃላችሁ፡ ሁለት ጊዜ፡ ሃያ-አምስት አልፎኛል። እና እንደበፊቱ አላስታውሰም፡ እና በብዙ ውጣ ውረዶችና፡ በየሰብሰባው እጅግ ቆስያለሁና።

7 የዛሬ ከሰአት በኋላ ርዕሳችን፡ **ምልክት** ነው። ታሪካችን ከግብጽ እንከፍታለን። ምሰሉ እጅግ የሚያምር ነው፡ ሁላችሁም እንድታዩት እና የምትችሉትን ያህል በትህትና እንድትሆኑ እፈልጋችኋለሁ። የታሪኩ ቦታ ግብጽ ናት፡ የታሪኩ ጊዜም በዘጸአት ጅማሬ ጊዜ ነው።

8 ይህም፡ አሁን፡ የዛሬው ዘመን ተምሳሌት ነው፡ እኛም ደግሞ ሌላ ዘጸአትን እየተጋፈጥን እንዳለ፡ የሚያሳይ ነው። እግዚአብሔር እሰራኤልን ከግብፅ፡ ወደ ተሰፋይቱ ምድር ማውጣቱ፡ ሙሽራይቱን ከቤተክርስቲያን ወደ ተሰፋይቱ ምድር ለማምጣት፡ የክርሰቶስ ተምሳሌት ነው። በሌላ ዘጸአት ላይ ነን። አሁን ቅዱሳት መጻሕፍትን የምታጠኑ ከሆነ፡ ከፍተኛ ቦታዎችን ለመምታት ጊዜ አለን፡ እውነት ነው። እኛ ማለት... እግዚአብሔር ሕዝብን ከሕዝብ እንዳወጣ፡ እግዚአብሔር ሙሽራይቱን ከቤተክርስቲያን ያወጣታል። ሙሽራይቱ ከሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ትጠራለች። በእግዚአብሔር የተመረጠ ትሆናለች፡ ትወጣለች። እኛም አሁን በዘጸአት ጠርዝ ላይ እንገኛለን፡ በዚያው ላይ የመቆማችን ማረጋገጫዎች ሁሉም የመጽሀፍ ቅዱሰ ቃሎች አሉን። አሁን፡ ያ ብዙ ጊዜ እንደተነገረ አውቃለሁ፡ ይሁን እንጂ፡ ወዳጆች ሆይ፡ ይህ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ይነገራል። ያኔ ጊዜ በዘላለማዊነት ይዋጣል። ሙሽራውን ከቤተ ክርሰቲያን ሊያወጣ እየመጣ ነውና።

9 በግብፅ እና በእሰራኤል መካከል በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን ልዩነት የፈጠረው ነገር፡ ያ ምልክት ነው። ሁሉም ሰዎች ነበሩ፡ ሁሉም አምላክ-የፈጠራቸው፡ የእግዚአብሔር የእጅ ሥራ ነበሩ፡ ልዩነታቸው ግን፡ የሞት ትእዛዝ በተላለፈ ጊዜ፡ በመካከላቸው የነበረ ብቸኛው ልዩነት ምልክት መኖሩ ነው።

10 አሁንም የእግዚአብሔር ልጅ በሚመጣ ጊዜ፡ ሙሽራይቱን ከቤተ ክርሰቲያን ሲያወጣት እንዲሁ ይሆናል፡ ልዩነታቸው ምልክት ይሆናል። አሁን፡ ዛሬ ከሰዓት በደንብ ተከታተሉና፡ ይህ እውነት ካልሆነ መርምሩ። ልዩነቱ ምልክት መኖሩ ነው። ልዩነት መኖር አለበትና።

11 አንድ ቀን፡ እግዚአብሔር በዓለም ላይ ይፈርዳል። የካቶሊክ ሰዎችን፡ "እሱ የሚፈርድባቸው ሁሉ፡ በምን ይፈርድባችኋል" ብዬ ብጠይቃቸው? "በቤተ ክርስቲያኒቱ፡" ይሉኛል። የትኛው ቤተ ክርሰቲያን? "የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን።" የትኛው የካቶሊክ ቤተ ክርሰቲያን? በርካቶች ናቸውና። ሜቶዲሰቶችም፡ "በሜቶዲሰት" ባሉኝ ነበር፡ ሰለዚህ ባፕቲሰቶች ከዚያ ውጭ ናቸው። ወይም፡ በባፕቲሰት ቤተ ክርሰቲያን ቢፈርድ፡ ሌሎቹ ሁሉ ውድቅ ናቸው። ጴንጤዎችም፡ "በጴንጤቆሰጤ" ቢሉ፡ ሌሎቹ ሁሉ ውድቅ ናቸው። እያችሁ፡ ግራ መጋባት ይሆናል፡ እጅግ ግራ መጋባት ይሆናል፡ እንዲህ ብሎ ማሰቡ፡ አእምሮን እጅግ ግራ ያጋባል።

12 እግዚአብሔር ግን ምድርን እፈርድባታለሁ ያለበት የራሱ መንገድ እዚህ ጋር አለ፡ በካቶሊክ ቤተክርሰቲያን አይደለም፡ በፕሮቴሰታንት ቤተክርሰቲያንም አይደለም። ነገር ግን ዓለምን በኢየሱሰ ክርሰቶሰ ይፈርዳል፡ ኢየሱሰም ቃል

ነው፡ ስለዚህ እንደገና ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ይመልሰናል። አያችሁ? ዓለምን በመጽሐፍ ቅዱስ ይፈርዳል። መጽሐፍ ቅዱስም የእግዚአብሔር የፍርድ መጽሐፍ ነው፡ መጽሐፉም የኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ መገለጥ ነው፡ አንዳች የማይቀነሰበት አንዳች የማይጨመርበት መጽሐፍ፥ ይህን ማድረግ ቅጣቱ፡ ስምህ ከሕይወት መጽሐፍ መደምሰስ ነው። ከመጽሐፉ ወዲያ ወዲህ አንበል፡ እግዚአብሔር የዚያ አካል እንዲያደርገን እንጸልይ።

13 አሁን ምልክት ማለት፡ ስንመለከተው፡ ምልክት ምንድነው? ምልክት፡ ምልክት ማለት አንድ ነገር ዋጋ የተከፈለበት ስለመሆኑ ማሳያው ነው። ልክ እንደ ባቡር ጣቢያ እና አውቶቡስ ተራ፡ ገንዘባችንን ይዘን ወደ ጣቢያው እንሄዳለን። አሁን፡ ተመልከቱ፡ ምልክት ብቻ ቢሚቀበሉበት፡ በአውቶቡስ ተራ ላይ፡ ገንዘብ መቀበል አይችሉም አይፈቀድላቸውም። ገንዘብ መቀበል አይችሉም፡ የሚቀበሉት ምልክት ነው፥ በአውሮፕላን፡ ብትሉም፡ በሌሎቹም ያው ነው። ወደ አንድ ቦታ ትሄዳላችሁ፡ ወደ ገንዘብ ተቀባዩ ሄዳችሁ፡ በገንዘባችሁ፡ የሆነ አይነት ምልክት፡ ብዙ ምልክቶችን፡ ትገዛላችሁ። እና ይህ ምልክት ክፍያችሁን መክፈላችሁን የሚያሳይ ማሳያ ነው። መርከቡ ላይ የመውጣት፡ አውሮፕላኑ ላይ የመውጣት መብት አላችሁ፡ የጉዞ ክፍያችሁን—መክፈላችሁ የሚያሳይ ምልክት ብቻ ያዙ እንጂ፡ በባስ መሳፈርም ይሁን፡ በሌላ መንገድ ሁሉ መብታችሁ ነው። አሁን ይህ አስታውሱ። እንዳትረሱት።

14 እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የጠየቃቸው... በግ እንዲያርዱ ነበር። ንጹሕ ምትክ እንዲሆን፡ ያህዌህ በግ እንዲያርዱ መስፈርት ጠየቀ። ባሳለፍነው ሳምንት እንዳሳለፍነው፡ እግዚአብሔር፡ አንዴ ውሳኔ ሲያደርግ፡ ፈጽሞ አይለውጠውም። መንገድም አዘጋጀ፡ ሊቤዠው ከፈለገና፡ ሰውን በንጹሕ ደም እንዲያድነው ከወሰነ በኋላ፡ ሰው በወደቀ ጊዜ ያደረገው የመጀመሪያ ሥራው፡ የሚመለሰበትን መንገድ ማዘጋጀት ነበር። ይህም ለዘለአለም ሲያደርገው ኖሯል። ፈጽሞ አይቀይረውም። እግዚአብሔር ከደሙ በታች በቀር፡ መሰዋእት አቅራቢውን የሚገናኝበት ሌላ ሰፍራ የለም። ብቸኛ ሰፍራው ያ ነውና።

15 በሥነ መለኮታችን፡ በቤተ እምነታችን ሥር፡ በትምህርት ፕሮግራማችን ሥር እንዲገናኘን ለማድረግ እንሞክራለን። አንዳንዶች ረጃጅም ግንቦች ገንብተዋል ሌሎችም ከተሞች፡ እነ ባቢሎን እና—የባቤል ግንብ፡ እና የተለያዩ ዓይነቶች ሰርተዋል። ይሁን እንጂ አሁንም እግዚአብሔር፡ እውነተኛውን መሰዋእት አቅራቢው የሚገናኘው ከደሙ ስር መሆኑ የጸና ነው። ፈጽሞ አይለውጠውም። ሁላችንም ሜቶዲስት መሆን አንችልም፡ ሁላችንም ጴንጤዎች መሆን አንችልም፡ ሁላችንም **ይህ፡ ያ፡** ወይም **ሌላ፡** መሆን አንችልም፣ አንስማማምና። ወደ አንድ ግለሰብ ስንመጣ ግን፡ የካቶሊክ ቄስ ይሁን ሌላም ይሁን፡ ወደ ደሙ ስር ከመጣ ወንድማማቾች ነን፡ የትም ይሁን ግድ የለኝም፡ ብቻ ከደሙ ስር ይገኝ።

16 አሁን፡ እስራኤል በግ ያርድ ዘንድ የያሕዌህ መስፈርት ነበረ፡ ደሙም ስራው እንደተሰራ የሚያሳይ ምልክት ነበረ። እግዚአብሔር ለመቤዠት፡ ከግብፅ፡ ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመሄድ፡ እንደ መስፈርት የታረደው እንስሳ ፈለገ። እንስሳውም እንዲህ ይሆናል... የታረደው እንስሳ ደሙ በበሩ ላይ እና በጉበኑ ላይ መቀባት አለበት፡ ይህም እግዚአብሔር የፈለገው መስፈርት እንደ ተፈጸመ ለምሥክርነት የቆመ ነው። አያችሁ? አሁን፡ ጠቦቱ አይደለም ምልክት የሆነው፡ ምልክት የሆነው ደሙ ነው። አሁን፡ ህይወት ከመሥዋዕቱ ወጥቷል፡ እና አሁን ደሙ

ምልክቱ ሆነ። ያዘዘው ትዕዛዝ ተፈጽሟል። ይህ አማኝ የተከለው ምልክት አድርግ የተባለውን መሰፈርት ማሟላቱ፡ ደሙ ምስክር ይሆናል፡ ይህ ነበር ምልክቱ። እሺ፡ አማኙን፡ አምልኮውን ማቅረቡ በማየት፡ ባቀረበው መሰዋዕት የታወቀ ይሆናል። አያችሁ?

17 ቤቱ **ይሄው** ነው፡ አምልኮ አቅራቢውም ይኸው፡ መሰፈርቱ ምን ነበር? "ጠቦት እረዱ። በአሰራአራተኛው ቀን በመሸ፡ እንከን—የሌለው ተባት፡ እሰራኤል ሁሉ ይረዱ፡ ደሙም ከሂሶጵ ጋር ተወሰዶ በበሩ ጉበን ላይ ይቀባ።"

18 እና፡ በነገራችን ላይ፡ ያ ሂሶጵ ተራ አረም ነበር። **ሂሶጵ** ማለት "እምነታችሁ" ነው። አንዳንድ ሰው ከተፈጥሮ በላይ የሆነ እምነት እንዲኖረው ይሞክራል፡ ፈውሳችሁ የሚያመልጣችሁ ለዚህ ነው። እምነት ቀላል ነገር ነው። ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመምጣት እምነት አገኛችሁ። ለመመለስም እምነት አገኛችሁ። መኪናህን ለማስነሣት እምነት አገኘህ። እራታችሁን ለመብላት በእምነት አገኛችሁ። እንደዚያ ነው፡ ቀለል ያለ እምነት። አሁን ደሙን ለመቀባት፡ በሂሶጵ ተቀባ። ይህም በፍልስጤም ውስጥ በየትኛውም ቦታ የሚበቅለው ተራ አረም ነው፡ ይህም ደሙ የሚቀባበት እምነት መሆኑን ያሳያል ይህንን ለማድረግ ሁሉንም ዓይነት የዶክተር ዲግሪ ማግኘት ያለባችሁ እጅግ የተካበደ ነገር አይደለም። እግዚአብሔርን ማመን፡ የተለመደ፡ የዕለት ተዕለት እምነት ነው። አያችሁ? በእምነት፡ "በሂሶጵ፡" "ደሙን ቀቡት።"

19 አሁን፡ እንግዲህ፡ አምልኮ አቅራቢው፡ በዚህ ደም ሥር ታይቶ፡ የያሕዌህን መሰፈርት እንደፈጸመ አሳይቷል፡ በዚህም ይታወቃል። ምልክቱ ያህዌህ ከጠየቀው የታረደው በግ ጋር መታወቁን ያሳያል። ሰራው ተሰርቷል። ዛሬም የክርሰቶሰ እና የአማኙ፡ እንዴት ያለ ፍጹም ተምሳሌት ነው። በአማኙ ላይ ምልክት ሲደረግበት፡ ተቀባይነት ማግኘቱን እና ሰራው እንደተሰራ ያሳያል።

20 ከዚያ በኋላ፡ ደሙ ራሱ፡ የመታወቂያው ምልክት ነው። እንሰሳው ሞተ፡ ደማም፡ ደሙም ግድግዳው ላይ ሆነ። አሁን፡ የእንሰሳት ህይወት፡ በደሙ ውስጥ ነው። ሕይወትም በደም ውስጥ ነው፡ ያንን እናውቃለን። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲሁ ይላልና፡ ሳይንሰም አረጋግጦታል፡ ሕይወት በደም ውስጥ ነው። ሰለዚህ እንሰሳው በታረደ ጊዜ፡ ነፍሱም ከእንሰሳው በተቆረሰ ጊዜ፡ ደሙ ምልክት ለመሆን፡ ኬሚሰትሪው ከደሙ የተነሰሣ መሆን አለበት። ምክንያቱ፡ በደም ውሰጥ ያለው ህይወት የእንሰሳት ህይወት ሰለሆነ፡ በአማኙ ላይ ተመልሶ ሊመጣ አይችልም።

21 እና የእንሰሳት ህይወት እና የሰው ህይወት ፈጽሞ የተለያዩ ናቸው። በውሰጡ፡ ምንም ነገር የለም። ደም ወሰዳችሁ፡ የእንሰሳውን ደም ብትጠቀሙ፡ ትሞታላችሁ። ሰለዚህ ተመልከቱ፡ በእኛ፡ በ—ሰዎች ዘንድ ያለው ደም በእንሰሶች ካለው ዘንድ የተለየ ነው፡ ምክንያቱም የሰው ልጅ ነፍሰ አለው። እንሰሳው ነፍሰ የለውም።

22 እና አሁንም፡ ሰለዚህ፡ ደሙ ራሱ፡ አሁን ይሄን ተረዱት፡ ቀይ ኬሚሰትሪው፡ የደሙ ኬሚካሎች፡ በጉ እንደሞተ ለማመልከት፡ በሩ ላይ መቀባት ነበረበት፡ እንጂ፡ የበጉ ሕይወት አምልኮ በሚያቀርበው ሰው ላይ ተመልሶ ሊመጣ አይችልም። ዛሬ ግን… ያ ተምሳሌት ብቻ ነበር።

23 ዛሬም የበጋችን፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ኬሚካላዊ ደም ሳይሆን፡ በደሙ ውስጥ የነበረው ያ ህይወት ነው፡ እርሱም መንፈስ ቅዱስ ነው። እርሱም እንደገና መጣ እኛም ተቀበልነው እግዚአብሔር እንድናደርገው የነገረንን በትክክል ያደረግነው ምልክት ይህ ነው። ከዚያ በኋላ፡ ምልክት በማድረጋችን፡ ከመስዋእታችን ጋራ የታወቁ እንሆናለን። በፍጹምነት። ከዚህ በላይ እንዴት ግልጽ ሊሆን እንደሚችል አይታየኝም። አያችሁ?

24 የደሙ ኬሚስትሪ በሮች ላይ ስለነበር፡ ደግሞ፡ ማንም ሰው ያ ቤት ከደሙ በታች እንደሆነ፡ ሊያውቅ ይችላል። እነሱም በዚያ አለፉ፡ የሞት መልአክ ደሙን ማየት እና መመልከት ነበረበት። አሁንም፡ እንደገና፡ የመንፈስ ቅዱስ ተምሳሌት ነበር።

25 አሁን፡ ተመልከቱ፡ የኢየሱስ ደም በተግባር በእያንዳንዳችን ላይ ሊቀባ አይችልም፡ ምክንያቱም በሰውነቱ ውስጥ የነበረው ደም ያ ብቻ ነው። ያም ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት፡ ከአካሉ ወጥቶ፡ ወደ መሬት፡ ተንጠባጥቧል፥ ያ ግን ለምልክት እንዲሆን አልነበረም። ምልክት የሆነው፡ በደሙ ውስጥ የነበረው ህይወት፡ ያንኑ ህይወት ነው። በአንድ ደቂቃ ውስጥ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ፡ አረጋግጥላችኋለሁ። ከመስዋዕታችን መታወቃችንን፡ እና የያሕዌ መስፈርት ማሟላታችንን ለማሳየት፡ በእያንዳንዳችን የሚመጣ ምልክት ነው።

26 ጴጥሮስ በበዓለ ሃምሳ፡ እንዲህ አለ፡ "ንስሐ ግቡ፡ እያንዳንዳችሁም፡ ለኃጢአት ስርየት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ። የተሰፋው ቃል ለእናንተና፡ ለልጆቻችሁ፡ ጌታ አምላካችን ለሚጠራቸውንም፡ በሩቅ ላሉት ሁሉ ነውና።" አያችሁ፡ ለእነርሱ በማሳየት አይደለ። "ጌታ ለሚጠራቸው ሁሉ።"

27 ብዙዎች ተጠርተናል ብለው ያስባሉ። ነገር ግን "ጌታ" የጠራቸው ሁሉ! "አስቀድሞ ያወቃቸውን፡ ጠራቸው፥ የጠራቸው ሁሉ፡ አጸደቃቸው፥ ያጸደቃቸው ሁሉ፡ አከበራቸው፡" ነገሩ ቀድሞ የተስተካከለ ነው።

28 ከዚያ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ለዘመናቸውም እንደሆነ የማያምኑ ሰዎችን ስታዩ፡ ምን እያደረጉ እንደሆነ አውቃችኋል? ከመስዋዕታችሁ ጋር የሚያገናኛችሁ ዋናው ምልክት እየካዱት ነው። ምን ለማለት እንደፈለግኩ ገብቷችኋል? አሁን እግዚአብሔር በጻፈበት መንገድ—ከተመለከታችሁት እጅግ ቀላል ነው። እኛን የተሸከመን ደሙ ነው… ይህም የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ፡ ያሳያል—እሱም ህይወት ነው።

29 አሁን፡ የእንስሳት ህይወት በሰው ውስጥ ተመልሶ ሊመጣ አይችልም፡ ምክንያቱም ሁለቱ አይዛመዱም፡ የእንስሳት ሕይወት በውስጡ ነፍስ የለውም። የሰው ሕይወት ነፍስ አለው። እንስሳው እርቃን መሆኑ አይገነዘብም። ትክክልና ስህተት ለይቶ አያውቅም። መ፡ መንፈስ ብቻ… አለው እንጂ—ነፍስ፡ የለውም። አሁን አስታውሱ፡ አሁን፡ እርግጥ ነው፡ ነፍስ የመንፈስ ተፈጥሮ ነች።

30 አሁን ተመልከቱት፡ የመሥዋዕታችን ሕይወት፡ የኢየሱስ ክርስቶስ፡ ደሙ በፈሰሰ ጊዜ… በአንድ ሰው ውስጥ፡ የታሸገ አምላክ ነበር። አሁን፡ ራሱን እንደ ሰው ሊያስተዋውቅ ስለፈለገ፡ የሰውን መልክ ለመያዝ፡ ከያሕዌነቱ ወረደ፡ እኛን ከሱ ጋር ያለን አንድነት ለማሳየት ነው። እርሱ የእግዚአብሔር በግ ነበር። ደሙም በሚገኝበት፡ በእርሱ በውስጡ…

31 አንድ ሰው አስታውሳለሁ “አይሁዳዊ ደም ነው፡” ብሎ ነበር። አይሁዶችም እንደዚያ ሲሉ ትሰማላችሁ። የአይሁድ ደም አይደለም፡ እንዲሁም የአሕዛብ ደም አይደለም። የእግዚአብሔር ደም ነው። አይሁዳዊም አይደለም… አይሁዳዊም አሕዛብም አይደለም። አምላክ ነበረ። “ድ—ድ—ድንግል ትጸንሳለች።”

32 አሁን፡ ብዙዎቻችሁ እና ፕሮቴስታንቶች ሁላችሁ እንቁላሉ የማርያም እንደሆነ እንደምታስቡ አውቃለሁ። እና የ—የሚመጣው ሄሞግሎቢን፡ ህይወት የሚመጣው በደም ሴሉ ላይ ነው። ምክንያቱም፡ ዶሮ ከወንዱ ጋር ሳትገናኝ፡ እንቁላል ልትጥል ትችላለች፡ ይህን እንጂ፡ ዘር ስለሌለው አይፈለፈልም። ሕይወት የሚመጣው ከደም ሥር ነው፡ እሱም ከወንድ ፆታ የሚመጣ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ግን የወንድ ፆታ አልነበረም፡ ስለዚህ፡ “በደም ውስጥ የነበረው ሕይወት፡” ከእግዚአብሔር ብቻ የመጣ ነው፡ እርሱም በማርያም ማኅፀን ውስጥ የደም ሕዋስ ፈጠረ፡ እግዚአብሔር ራሱ፡ ፈጣሪ ራሱ፡ የደም ሕዋስ ፈጠረ። አሁን ተመልከቱ። “አይ፡ እሱ አካል ነበር። ማርያም እንቁላል ነበራት፡” ይላሉ። አይደለም፡ ወዳጄ። አይደለም፥ በእንቁላሏ አይደለም። እንቁላል ከሆነ'ማ፡ ያለ ስጋዊ ፍትወት የወንድ የዘር ፍሬን ማግኘት አይቻልም። እንግዲህ እሱ፡ እሷ ስሜት ከነበራት፡ እግዚአብሔር ምን ስራ ልትሉ ነው?

33 እንቁላሉና ደም ሁለቱም ፈጠራቸው። የነበረው በትክክል ያ ነው። “እግዚአብሔርን ዳሰነዋል፡” መጽሐፍ ቅዱስ። አንደኛ ጢሞቴዎስ 3:16 ላይ፡ “እግዚአብሔርን የመምሰል ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፥ እግዚአብሔር በሥጋ ተገለጠ። በእጃችን ዳሰነዋል።” ያ አካል እግዚአብሔር ነበር። በእርግጠኛነት፡ ነበር። እርሱ ሙሉ በሙሉ በሰው አምሳል የሆነ፡ አምላክ ነበር።

34 አሁን በዚህ ውስጥ እንደተገነዘብነው፡ ያ የደም ሕዋስ ከተቆረሰ በኋላ፡ እግዚአብሔር ተለቀቀ። “እግዚአብሄር በክርስቶስ ሆኖ፡ ዓለምን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር።” ይህም፡ በሌላ በማንም ሊደረግ አይችልም፡ ሌላ ሊደረግ አይችልም፥ ያንን ቅዱስ ደም ራሱ፡ ይጠይቃል። እግዚአብሔር የራሱን ሕግ መከራ ለመቀበል፡ ወርዶ ሰው መሆን ነበረበት። ኢየሱስ ከእግዚአብሔር የተለየ ሰው ከሆነ፡ እና እንዲሁ ነብይ ከነበረ፡ እንግዲያውስ እግዚአብሔር ፍትሐዊ አይደለም።

35 ምሳሌ “ቢሊ ሊገደልበት በሚገባው ኃጢአት ወንድም ግራንት ይሙት፡” ካልኩኝ፡ ወይም በሌላ ነገር፡ ቅጣት ባለበት ነገር እንዲህ ካልኩኝ፡ ይህ ፍትሐዊነት አይደለም። እኔ በተናገርኩት በቅጣቴ የገዛ ልጄ የሚሞት ከሆነም፡ ፍትሐዊነት አይደለም። ማድረግ የምችላት አንዲት ፍትሕ አለች፡ እሱን ማዳን ከፈለግኩኝ፡ ሰፍራውን እኔ በመውሰድ ነው።

36 የኃጢአተኛውን ቦታ ይይዝ ዘንድ፡ እግዚአብሔር ሥጋ መሆን ነበረበት፥ እግዚአብሔር በሥጋ ተገለጠ ማለት፡ ከራሱ ከእግዚአብሔር ሌላ ምንም የለም። እንግዲህ፡ እርሱ፡ በሥጋ የተገለጠው፡ የዓለምን ኃጢአት ሊያስወግድ ነው። እኛ በእርሱም እንታወቅ ዘንድ፡ በእኛ ውስጥ ራሱን አስታወቀ። ዓላማውን ተመልከታችሁት?

37 አሁን መታወቂያችንን ከመሥዋዕታችን ጋር ሆኖ አግኝተነዋል፡ በውስጣችን ያለው የመሥዋዕት ሕይወት፡ እርሱም መንፈስ ቅዱስ ነው። ስለዚህ ህዋሱ በተቆረሰ ጊዜ፡ እግዚአብሔርን ለቀቀ፡ እግዚአብሔር ተለቀቀ፡ ሕዝቡን በደሙ እንደ ቀደሰ እግዚአብሔርንም እንደገና በሰው ውስጥ እንዳስገባ አስታወቀ። አምላክ በውጣችሁ፡ የዘላለም ሕይወት!

38 እና የትኛውም የግሪክ ምሁር የዘላለም ሕይወት የሚለውን ቃል፡ ከየት እንደመጣ ያውቃል፡ ማለት ከ Z-o-e፡ **ከዞዊ** የመጣ መሆኑን ያውቃል፡ ይህ ማለት “የእግዚአብሔር የራሱ ሕይወት” ነው። በትክክል። ሕይወት ማግኘት የምትችሉበት ብቸኛው መንገድ ይህ ነው፡ የዘላለም ሕይወት አንድ ብቻ ናት፡ ያም በውስጣችሁ የሚኖረው የእግዚአብሔር ሕይወት ነው። አያችሁ? ያን ጊዜ የዘለአለም ህይወት አላችሁ፡ ምክንያቱ ብቸኛው የዘለአለም ይህ ብቻ ነው። እኛ ደግሞ የዓለም ወይም የማንኛውም ነገር መሰረት ሳይፈጠር በፊት፡ የአሳቡ መገለጫዎች ነን። ይህ ሁሉ የእሱ አሳቡ ነው፡ እኛም የእሱ አሳቦች ምን እንደነበሩ ማሳያዎች ነን።

39 ኃጢአትንም ለማስወገድ መውረድ ነበረበት። ሌላ ማንም ሊሰራው አልቻለም። ሊያደርገው የሚገባ ማንም አልነበረም። ከእርሱ በቀር ማንም ሊሰራው አይችልምና፡ አደረገው።

40 ከዚያም፡ ያ ሕይወት ከዚያ አካል፡ ከዚያ ሰው በተለቀቀ ጊዜ፡ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ ነው (በመፍጠር ኃይሉ እንደ ማንኛውም ኮንትራክተር፡ ሕንፃ ሠራ፡ እግዚአብሔር ራሱ እንዲሁ አደረገ፡ የሚገባበት የመኖሪያው ህንጻ፡ በራሱ ሠራ።)፡ ከዚያም፡ ያ ሕይወት በታረደ ጊዜ፡ ደሙ፡ ኬሚስትሪው፡ የአቤል ደም በምድር ላይ **እንደ** ፈሰሰ፡ በድምር ላይ ፈሰሰ፡ ከዚያ ደም ግን የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ወጣ፡ ይህም በጴንጤቆስጤ ቀን ለሰዎች የተላከው ነው፡ ይህን ለእነርሱ ከሞተው መሰዋዕት ጋር የታወቁ ይሆኑ ዘንድ ነው። በዓለም ላይ ሌላ የምናገኝበት መንገድ የለም። ትክክለኛው ምልክት!

41 ለምሳሌ፡ የሞት ፍርደኛ ከተባላችሁ፡ እና በኤሌክትሪክ ወንበር እንደምትገደሉ ካወቃችሁ፡ እስኪ አስቡት፡ ማለት...

42 ዳላስ ሆይ፡ ሰሚ! የደሙ ምልክት የሆነውን የኢየሱስ ክርስቶስን ደም አልቀበልም ማለት፡ አይታችሁት አልፈልግም በማለታችሁ፡ ደሙን በእጃችሁ እንደያዛችሁት ፍርዱን ትጋፈጣላችሁ። አንተ ኃጢአተኛ፡ የቤተ ክርስቲያን አባል ሆይ፡ ይሄን አስብ።

43 ሊ ኦስዋልድ፡ ፕሬዚዳንቱን ከመግደሉ የተነሣ፡ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፊት ለፊት ቀርቦ ያላበው ያንን ላብ ሁሉ፥ ቅንጣት ምህረት እንደማያስገኝለት፡ ከጥቂት ቀናት በፊት፡ ባወቀ ጊዜ፡ ያ ሰው ምን ተሰምቶት ይሆን! እጅግ የሚያስፈራ ገጠመኝ ነው። ይህን አይገባውም ነበር፡ የገደለው ሌላኛው ሰውዬ ነውና። የወገንህ ደም ማለት የዩናይትድ ስቴትስ ፕረዚዳንት ደም፡ በእጅህ ላይ ሆኖ፡ በተቆጣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፊት ለፊት ቁጭ ማለት እስኪ አስቡት! በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ላላፋችሁ ሰዎች፡ በእግዚአብሔር ፍርድ ፊት ስትቆሙ፡ ይህ ለእናንተ ቀላል ይሆንላችኋል። ስታውቁት ላይ ያስጠምቃል። ኦስዋልድ ከዚህ ህይወት ከመለየት በቀር ሌላ አማርጭ አልነበረውም፡

እግዚአብሔር ግን እናንተን ከህልውናው ለዘለአለም ይለያችኋል። ያን ጊዜ አስቃቂ ይሆናል። ልብ በሉ።

44 ጥፋተኛ ተብላችሁ፡ ፍርድ ቤት ውስጥ ከቀረባችሁ፡ አለ የተባለው ጠበቃ መፈለጋችሁ አይቀርም። ሰው ሁሉ የሚያደርገው ነው።

45 እና በዓለም ውስጥ የተወለደ እያንዳንዱ ሰው፡ ከምን አይነት መልካም ቤተሰብ ይወለድ አይገደኝም፡ የኢየሱስ ክርስቶስን የደሙ ይቅርታ እስኪቀበል ድረስ በደለኛ ነው። እና ይቅርታውን የምታውቁበት ብቸኛው መንገድም ይህ ነው፡ ምልክቱ ራሱ በእናንተ ላይ ሲሆን፡ እና ምልክቱ ሲኖራችሁ ነው።

46 ልብ በሉ፡ ጥፋተኛ ተብላችኋል፡ ከዚያ በኋላ ክሳችሁን የሚሟገትላችሁ አለ የተባለውን ጠበቃ አደን ትወጣላችሁ። እኔም ወደ እግዚአብሔር ፍርድ ፊት እየሄድኩ ከሆነ፡ ቄስ አልፈልግም፡ ሌላ ሰውም አልፈልግም፥ ክሴን የሚሟገትልኝ አለ የተባለውን ጠበቃ እፈልጋለሁ።

47 ለእናንተ፡ የክርስቲያን ወዳጆቼ ሆይ፡ እንዲህ እላለሁ። ጠበቃችን ዳኛችን ጭምር ነው፡ እና ዳ—ዳኛችን ጠበቃችንም ሆኗልና። ምህረቱን ስንቀበል ክሳችን ተቋርጧል። ዳኛው ራሱ ወርዶ ጠበቃ ሆነ፡ ጠበቃውም ዳኛውም አንድ አካል ነው። በእርሱ ላይ ባኖረው በራሱ ሞት ሰውን ያጸድቅ ዘንድ፡ እግዚአብሔር ሰው ሆነ። ሃሌ ሉያ! ይህም ማለት፡ "አምላካችንን አመሰግኑት!" ምስጋና ሁሉ ይገባዋል። ዳኛችን እና ጠበቃችን አንድ ሰው ነውና።

48 መንፈስ ቅዱስም ይቅር መባላችን የሚያሳይ ምልክት ነው። ክሱ ተዘግቷል። የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት በትክክል የተቀበለ ወንድና ሴት ሁሉ፡ ተፈትኖ አልፏል፡ ከጠበቃው፡ ከዳኛው ጋር የታወቀ ሆኗል፡ ከመሥዋዕቱ ጋር የታወቀ ሆኗል፡ እና በርሰቱ የያዘው ምልክት ወደ ክብር ጉዞው እንደተከፈለ ያሳያል። አሜን። ሁሉም ነገር አልቋል። ያንን ምልክት ይዟልና። የኢየሱስ የትንሣኤው ምስክር የሆነው፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ የእሱ ነው። አሜን። ታምናላችሁ? [ጉባኤው "ኣሜን፡" አለ።—እርታዒ።] ምልክቱን መያዛችሁ፡ ይህ የእናንተ መታወቂያ ነው።

49 ምልክቱን ካልያዛችሁ፡ አትገቡም። ምልክቱ መያዝ አለባችሁ። የክፍያው መስፈርት ያ ነው፡ "ደሙን ሳይ፡ ደሙ ምልክት ይሆናል። ደሙን ባየሁ ጊዜ፡ አልፋችኋለሁ።" ምልክት አድርጉ። ካላደረጋችሁ ግን፡ ይኸው፡ አታመልጡም። ምልክት ማድረግ አለባችሁ።

50 ምልክቱ ካልታየ፡ ምልክቱ በዚያ ባለመታየቱ ምክንያት፡ ኪዳኑም ጥቅም ላይ አይውልም። አሁን እናንተ "አንዴ፡ ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ቆይ እስኪ፡ አንዴ፡" ትሉኛላችሁ። ይህ በትክክል እውነት ነው።

51 ያ ምልክት ከቃል ኪዳኑ በላይ ነበርና። እስራኤልም የመገረዝ ቃል ኪዳን ተሰጥቷቸው ነበርና፡ እና ማንኛውም አይሁዳዊ ወጥቶ ማንኛውንም አካል እንዲህ ማሳየት ይችላልና፡ "እኔ የተገረዝሁ፡ አይሁዳዊ ነኝ፡ እንደ ያህዌ ትእዛዝ የተገረዝሁ መሆኔን ላረጋግጥላችሁ እችላለሁ፡" ይሁን እንጂ ምልክቱ ባይኖረውም እያስባርረውም። ምልክቱን ማሳየት አለበት። ገባችሁ ወይ? [ጉባኤው "ኣሜን፡" አለ።—እርታዒ።] ምንም ይሁን፡ ምልክቱ... ማድረግ አለበት። እናንተም በቃል ኪዳኑ ውስጥ ሆናችሁ... ማንም አይሁዳዊ፡ "በበሬ ላይ ምንም ደም አልቀባም፡ እኔ የቃል ኪዳን አይሁዳዊ መሆኔን ማረጋገጥ

እችላለሁ፡” ቢል የሞት መልአክ ያገኘዋል። የቱንም ያህል ታማኝ ቢሆን፡ ምን ያህል የቤተ ክርስቲያን አባል ቢሆን፡ ምን ያህል አሥራት ከፋይ ቢሆን፡ ምን ያህል ያሕዌህን እምናለው ይበል፡ የያሕዌህ መሰፈርት ያንን ምልክት ነው።

52 ዛሬም፡ እንዲሁ ያደርጋል። መሆንም አለበት። መሆን አለበት፡ “ከሰማይ በታች ሌላ መንገድ የለምና፡ ሌላም የተሰጠ ሰም የለም፡ በምንም መንገድ፡” ምንም ያህል ጥሩ፡ ምን ያህል ታማኝ ይሁን። ምልክት መኖር አለበት፡ መታየት አለበት።

53 እንዲህም ብትሉስ፡ “ደሙ፡” “አይ፡ በጉን አርጄ ማሰሮ ውስጥ አስቀመጥኩት። እዚህ አዘጋጅቼዋለሁ።” ያለው እንዲህ አይደለም። በበሩ እና በጉበኑ መሆን አለበት። መታየት አለበት።

54 እናንተም ህይወታችሁ ምልክቱን የሚያሳይ ይሁን። እናንተ፡ ጴንጤዎች ሆይ፡ ምን ነካችሁ? የተቆራረጠ ፀጉር፡ የተቀባቡ ፊቶች፡ ወንዶችም፡ ቆሻሻ ቀልዶች እና ሌሎች፡ የጌታዬ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም የመንፈስ ቅዱስ የሚታይ ምልክት መሆኑ የት አለ? እናንተ፡ የአምልኮት መልክ ያላችሁ፡ “ጥንቆላ ነው” ወዘተረፈ የምትሉት፡ የእግዚአብሔርን ሥራዎች፡ “ጥንቆላ” ትሉታላችሁ። ምልክትን እንዴት ታሳያላችሁ?

55 “እኔ ጴንጤ ነኝ-… ” ይላል፡ ምንም ሁን አይገደኝም። “ባፕቲስት ነኝ። ፕሬስ-… ” ምን ሁን ግድ የለኝም። ምልክት በቦታው መሆን አለበት። እግዚአብሔር የሚፈልገው ይህ ነው፡ ከዚያ በቀር ሌላ ምንም ነገር አይፈልግም።

56 “እኔ’ኮ፡ ዶክትሬት ተምሬአለሁ፡” ትላለህ። ስንት ዲግሪ ይኑርህ አይገደኝም። የእግዚአብሔር መሰፈርት ያንን ምልክት፡ ብቻ ነው። ጉዞህ መከፈሉ የሚያሳይ ተምሳሌት ነው። ዝናህ ወይም ሌላ ነገር አይቀበልም። ያንን ምልክት ያስፈልጋል።

57 የአውቶቡስ ሹፌር “ይኸው፡ ቆይ፡ ያ የእኔ ምልክት አይደለም፡” ይላል።

58 ባለ አውሮፕላኑም “እሺ፡ ዞር በል፡” ይልሃል። ትኬቱ ምልክት ነውና። እስኪ ሂድና ወደ ፓይለቱ ቀርበህ እንዲህ በል፡ “ይኸው፡ የአውሮፕላን ክፍያ ልክፈልህ። ስንት ነው? ”

“ሂድና ምልክትህ ግዛ።”

“ኡህ፡ እክፈልሃለሁ’ኮ።”

59 “አልቀበልህም። ክፍያውን ከፍለህ ምልክት እስክታመጣ ድረስ ወደ አውሮፕላኔ አትገባም። እኔ የምጠብቀው ምልክት ነውና።”

ትላላችሁም፡ “እኔ’ኮ፡ የተማረ ሰው ነኝ። **ይሄን** አድርጌአለሁ። እኔ… ፡”

60 ምንም አድርግ አይገደኝም፡ ምልክት ከሌለህ አትሳፈርም። አሜን እና አሜን። አይታያችሁም? የእግዚአብሔር መሰፈርት ምልክት ነው። “ደሙን ባየሁ ጊዜ፡ እና ምልክቱን ባየሁ ጊዜ ብቻ አልፋችኋለሁ።”

61 ካልታየ ግን፡ ቃል ኪዳኑ ጥቅም የለውም። አንድ አይሁዳዊ ወንድሞችን ጠርቶ—ይኸው እኔ የተገረዝኩ አይሁዳዊ ነኝ በማለት፡ መሆኑን በፍጹም

ማረጋገጥ ይችላል፡ “ተመልከቱ፡ እኔ የተገረዝኩ ነኝ።” ያ ማለት ምንም አይጠቅምም።

62 “እኔ ሜቶዲስት ነኝ። ባፕቲስት ነኝ። እኔ ጴንጤ ነኝ። እኔ **ይህ** ነኝ። እኔ **ያ** ነኝ፡” ትላላችሁ። ይሁ ሁሉ ከንቱ ነው።

63 ምልክት ይኑራችሁ። ምልክቱ ሲመጣም፡ ስለ ክርስቶስ ይመሰክራል። እንደሚሆን ተናግሯልና። ክርስቶስም ቃል ነው። እና መጽሐፍ ቅዱስ በከፊሉ እውነት ነው፡ ብላችሁ እየካዳችሁ፡ ምልክቱ የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር ሆኖ ሳለ፡ ምልክት አለኝ እንዴት ትላላችሁ? አያችሁ፡ እኔ የሚገርመኝ ይህ ነው።

64 “ኦህ፡” “የተአምራት ዘመን… እኔ አላምንም፡” ኦህ፡ እስኪ ተመልከቱት፡ ምልክት የለውም፡ ትላላችሁ። ምልክቱ እያንዳንዱን ቃል፡ ሁሉንም በ “አሜን” ያጸናዋል፡ ምክንያቱም እሱ ራሱ እግዚአብሔር ነው። አያችሁ? በጣም ጥሩ።

65 ይሁን እንጂ ምልክት ከሌለ፡ ቃል ኪዳኑ ጥቅም አልባ ነው። ያኔ ተሰርዟልና። አሁንም ያው ነው! ምንም ቢሆን—ምንም ያህል፡ “በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን ቃል ሁሉ አምናለሁ፡” ብትልም እንኳ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ እኔ—መጽሐፍ ቅዱስ ግማሹን፡ መላውን መጽሐፍ ቅዱስ፡ በልቤ ልጠቅስልህ እችላለሁ። ሁሉንም ነገር አምናለሁ፡” ማለት ትችላላችሁ። መልካም። ሰይጣንም፡ ይጠቅሳል። ኧሃ-ሃህ። መሰፈርቱ ምልክት ነው!

66 “ይኸውልህ፡ ወንድም ብራንሃም፡ ግድግዳዬ በዲግሪ የተሞላ ነው። የባችለር ኦፍ አርት አለኝ፡ የዶክትሪት ዲግሪ አለኝ፡ በላቲንኛም፡ ኤልኤልዲ አለኝ። እና፡ ብዙ፡ መጻሕፍት ጽፌአለሁ። ይሄን አድርጌአለሁ። ያላረኩት የለም። እነዚህን ሁሉ—ሰርቻለሁ።” ምንም አይገደኝም። ይህ ሁሉ ይሁን፡ አሁንም ግን ምልክት ያስፈልግሃል። ምልክት፡ መሰፈርቱ ምልክት ነውና!

67 “የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ነኝ። እ—እኔ ጥሩ ሰው ነኝ። እኔ **ይህ፡ ያ** ነኝ፡” ትላላችሁ። ያ ጥሩ ሊሆን ይችላል፡ ያ ሁሉ ጥሩ ነው፡ ግን አሁንም ምልክት ሊኖርህ ይገባል!

68 አሁን፡ የሞት መቅሰፍት በማንኛውም ጊዜ ግብፅን ለመምታት ተዘጋጅቷል፡ እንዲሁም ሞት ይህችን አገር በማንኛውም ጊዜ ሊቀስፋት ተዘጋጅቷል።

69 እና ጄን፡ የሆነ ጊዜ ላይ አባትሽ የተናገረው አስተያየት፡ ትዝ ይለኛል። ሁልጊዜም ደስ ይለኛል። እንዲህም አለ፡ “እግዚአብሔር አሜሪካን ስለ ስራዋ ዝም የሚላት ከሆነ፡ ታውቃላችሁ፡ ይህች አገር፡ እስከነ ተመሳሳይ ኃጢአትዋ ዝም ካላት፡ ሰዶምና ገሞራን አስነስቶ ስለ አቃጠላቸው፡ ይቅርታ የመጠየቅ የሞራል ግዴታ አለበት።” በትክክልም እውነት ነው።

70 አስታውሱ፡ እስራኤል ስለ ሠራችው ኃጢአት ሁሉ ተከፍሏታል፡ እኛም ይከፈለናል። ምን ያህል ልቅ እየሆንን ነው? ጋሻውን ጠበቅ አርጉ! ቤተ ክርስቲያን ሆይ፡ ወደ እግዚአብሔር ተመለሺ! ይህን የምለው የተለየ ለመምሰል አይደለም። እንደ ማስጠንቀቂያ እየነገርኳችሁ ነው። እመኑት!

71 የሞት መቅሰፍት ተዘጋጅቶ ነበር። እግዚአብሔር ጸጋውንና ምሕረቱን፡ በኃይልና በምልክቶች በድንቅም አሳያቸው (ዛሬም ቤተክርስቲያንን ከማውጣቱ በፊት እንዲሁ አሳየ)፡ ቢሆንም ንስሐ ለመግባትና መልእክቱን ለማመን እምቢ አሉ።

72 እያችሁ፡ ቤተ ክርስቲያን ከመውጣቷ ጥቂት ቀደም ብሎ መልእክት ነበር። ሁልጊዜም እንዲሁ ይሆናል። አሁን ተመሳሳይ ነው። ማንኛውም መንፈሳዊ ክስተት ከእግዚአብሔር ዘንድ ምልክት ነው። ይህን ታምናላችሁ? [ጉባኤው “ኣሜን፡” አለ።—እርታዒ።] ልክ እንደ መልእክቱ፡ ምልክት ይቀድማል በመቀጠል ምልክቱን ተከትሎ መልእክቱ ይመጣል። እግዚአብሔር ለሙሴ፡ እንዲህ ብሎ ነገረው፡ “የመጀመሪያውን የምልክቱ ድምጽ ካላመኑ፡ ምናልባት የሁለተኛውን ምልክት ድምጽ ያምናሉ።”

73 አሁን፡ ምልክቱ ሲከሰት አይታችሁ፡ ከኋላው ተከታይ መልእክት ከሌለው፡ የተለመደና ያረጀ የቲኦሎጂ ጉዳይ ነው፡ ያ ከእግዚአብሔር ዘንድ አልነበረም። ነገር ግን ምልክት ባለበት ቦታ ሁሉ፡ መልእክት ደግሞ ይከተላል። አሁን ተመልከቱ። ኢየሱስ ወደ እይታ በወጣ ጊዜ...

74 አደነቆርኳችሁ እንዴ? ማይክሮፎኑ ላይ የሚነገር ነገር፡ እየተመለሰ ይመስላል። ምናልባት ትንሽ ጩኸት በዝቶበት ይሆናል። እንድትረዱት እፈልጋለሁና።

75 ኢየሱስ ወደ እይታ በወጣ ጊዜ፡ ያን ያህል ከሰዎች ጋር አይነጋገርም ነበር፡ ሰዎች ሁሉ ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው እንዲገባ ይፈልጉት ነበር። “ኦህ፡ ይህ ወጣት ነቢይ በማግኘታችን፡ በጣም ዕድለኞች ነን።” የታመሙትን እየፈወሰ ነበር። “ኦህ፡ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን። እግዚአብሔር ታላቅ ሰው አስነሳልን።” ጥሩ ነበር። ይህም ምልክቱ ነበር... ስለዚህ አንድ ቀን ወደ አንድ ሁኔታ ላይ ደረሰ።

76 ኢሳይያስ 35 ላይ ምልክት ይሆናል ብሏል። “በዚያን ጊዜ አንካሳ እንደ ሚዳቋ ይዘልላል፡” ወዘተ፡ “የዕውሮች ዓይን ይገለጣል።” ምልክት ነበር።

77 እንደ መሲህ እና ሌላ ሌላ፡ ምልክቱን አሳይቷል። ሰዎቹም፡ ብዙዎቹ፡ “አዎን፡ ይሄን እቀበላለሁ፡” ይሉ ነበር። እንግዲህ፡ አሁን፡ ያ ምልክት ከሆነ፡ የድምጹ ምልክት ይኖር ዘንድ ተገቢ ነው። ከኋላው የተከተለው ድምፅ ምን ነበር? ትምህርቱን ማስተማር ሲጀምር እና የሳር ውስጥ እባቦች ናችሁ ባላቸው ጊዜ ነው። ድምፁ ከምልክት ጋር በመጣ ጊዜ፡ እያችሁ፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እንጋፋ አልነበረም። በመጀመሪያ ምልክቱ ቀደመ።

78 ሙሴም ምልክት ይዞ ወደ ግብፅ ወረደ። በትሩንም በጣለ ጊዜ፡ እባብ ሆነች። ያ ምልክት ነበር። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን፡ ድምፁ ከምልክቱ ጋር መጣ። ያኔ የተለየ ነበር። እያችሁ፡ ያንን አይፈልጉትም። ድ—ድምጹ፡ ምልክቱን፡ መከተል አለበት። ቅዱሳት መጻሕፍት የሚፈጸሙበት ጊዜ ስለነበር፡ ከዚያ ጊዜ በቀር ሌላ ጊዜ ሊመጣ አይችልም ነበር። በሚቃጠል ቁጥቋጦ ውስጥ፡ የነገረውን ተመልከቱ፡ “በግብፅ ያለውን የሕዝቤን መከራ በእውነት አየሁ፡ ከአስገባሪዎቻቸውም የተነሣ ጩኸታቸውን አይቻለሁ፡ ለአብርሃምም የገባሁትን ቃል ኪዳኔን አሰብሁ።” ወደ ግብጽ እንደሚወርዱ ለአብርሃም ነግሮታል፡ አራት መቶ ዓመታት አልፈዋል። እያችሁ፡ ሌላ ዘመን ሊሆን አይችልም። በዚያን ጊዜ ሙሴ መምጣት ነበረበት።

79 የእግዚአብሔር ትልቁ ሰዓት ፍጹም ነው። አንድ ደቂቃ አይፈጥንም ወይም አንድ ደቂቃ ወደ ኋላ አይሆንም። ልክ በሰዓቱ ይሆናል። እና፡ ስለዚህ፡ እያችሁ፡ ሁሉም ነገር በትክክል እየሄደ ነበር፡ በሌላ ዘመን ሊመጣ አይችልም።

80 እነዚህ ነገሮችም በሌላ ጊዜ ሊመጡ አይችሉም። ይህ በሉተር ዘመን ሊመጣ አይችልም ነበር። በዌስሊ ዘመን ሊመጣ አይችልም ነበር። የባፕቲስቶች ወይም የሜቶዲስት ቀናት ላይ፡ በዘመናቸው፡ ሊመጣ አይችልም። አሁን መምጣት ነበረበት። እስራኤል ሀገር መሆን ነበረባት። አብያተ ክርስቲያናትም አሁን እንዳሉበት መሆን አለባቸው። ሦስተኛው መልእክት፡ ሦስተኛው የቤተ ክርስቲያን ዘመን መኖር ነበረበት። ሎዶቅያ መሆን ነበረበት። ጴንጤቆስጤ እስኪመጣ ድረስ መጥቶም ጉዳያቸውን ሰርተው፡ ተደራጅተው የሚያደርጉትን እስካላደረጉት ድረስ፡ ሊሆን አይችልም ነበር። ከዚያ በኋላ እርሱን፡ ጌታን ከቤተክርስቲያን ሲያስወጡት፡ ያን ጊዜ ይመጣል። እርሱ ቃል ነውና።

81 ቃሉን በየትኛውም ቦታ መጋፈጥ ይፈራሉ። ስለ እሱ በጣም ዝም ይላሉ፡ ነገር ግን ደግሞ ይጎርራሉ።

82 እዚህ በአንድ ወቅት፡ በቺካጎ፡ እግዚአብሔር ራእይ አሳየኝ። እዚያም ሦስት መቶ አገልጋዮች ነበሩ። ስለ እባብ ዘር፡ እና ስለ ሌሎች ጉዳዮች ነበርና፡ “አሁን ምን እንደፈለጋችሁ አውቄአለሁና… ” አልኳቸው፡ “ከእናንተ አንዱ መጽሐፍ ቅዱሱን ይዞ ይምጣና መጥቶ ከጎኔ ቆሞ ልክ አይደለህም ይበለኝ፡” አልኳቸው። እንደዚያ አይነት ዝምታ አይታችሁ አታውቁም። እኔም እንዲህ አልኳቸው፡ “እንግዲያውስ እረፉ አትከታተሉኝ።” አያችሁ፡ ከአስተሳሰባቸው ትምህርት ውጪ ነው።

83 ሆኖም፡ እንዲህ ይላሉ፡ “ወንድም ብራንሃም በተቀባ ጊዜ ነቢይ ነው፡ ቅባቱ ሲለየው ግን፡ ኡህ፡ እንጃ።” ምን አይነት… ይህ ድብልቅልቅ-ያለ የ—የ—የ— የቲኦሎጂያን ምልክት አይደለምን! ይህ…

84 **ነቢይ** የሚለው ቃል ትርጉሙ “የቃሉን መለኮታዊ ገላጭ” ማለት ነው። የጌታ ቃል ወደ ነቢያት ይመጣል። ኢየሱስ የታወቀው በዚህ መንገድ ነው። ከትንሣኤ በኋላም፡ እንዲህ አሉ፡ “የእግዚአብሔር ነቢይ እንደነበረ አወቅን፡” አያችሁ፡ “እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆን በቀር ማንም ሰው እነዚህን ነገሮች ሊያደርግ አይችልም።” ከዚያ በኋላ ግን መልእክቱን መቀበል አልፈለጉም። ዮሐንስም ነብይ ነበር፡ መልእክቱን መቀበል አልፈለጉም። ማናቸውም፡ ኤልያስን መቀበል አልፈለጉም፡ መለኮታዊ መገለጥ ግን አግኝተው ነበር።

85 ቃሉ፡ የእንግሊዘኛው ቃል፡ **ነብይ፡** በእንግሊዘኛ ቃላቶች ብዙ ትርጉም ይኖረዋል “ሰባኪ፡” ማለትም ነው። የብሉይ መጽሐፍ ቅዱስ **ነቢይ** ስትሉ ግን፡ ትርጉሙ “ባለ ራእይ፡” ማለት ነው። ምስክርነቱም፡ የተናገረው ነገር በመፈጸሙ ነበር፡ ይህም፡ እርሱ ነቢይ ለመሆኑ ማሳያ ነበር፥ እርሱም ደግሞ ከተጻፈው ቃል ዘንድ መለኮታዊ መገለጥ እንዳለው ምልክት ነው። ከዚያም እግዚአብሔር፡ ከበስተጀርባው አረጋግጦለታል፡ መስክሮለታል።

86 እንዴት? እሺ፡ በዚህ መንገድ ብቻ መሆን አለበት፡ ይህ ነው። ምንም ዳር ዳር ማለት አያስፈልግም። እግዚአብሔር እንደዚያ ይሆናል ብሎ ተናግሯል፡ ይኸው። እና ዛሬ ግን፡ አያችሁ፡ ቃሉን የሚሳውቅ እውነት ስለመሆኑ የሚመሰክር፡ ምልክት መኖር አለበት። ከዚያም ቃል እንዴት ገባ፡ የተሰፋይቱን-ምድር ሕዝብ ሁሉ እንዴት አዘጋጀ፡ እንግዲህ፡ ይህ ተምሣሌት የነበረውን፡ የዘጸአት ጉዞ ጀመረው።

87 አሁን ከመልእክቱ ጋር፡ ሌላ አስራ አምስት፡ ሃያ ደቂቃ ለመቆየት እሞክራለሁ። አሁን በደንብ ልብ በሉ፡ ይህን እንዲገባችሁ እፈልጋለሁ፡ ከዚህ በኋላ ላላገኛችሁ እችላለሁና፡ እያችሁ።

ልብ በሉ፡ አሁን ህዝቡን እንዴት እንዳዘጋጀ ተመልከቱ።

88 መንገዱን እንደማይለውጠው ስንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? በፍጹም አይለውጥም። [ጉባኤው “ኣሜን፡” አለ።—አርታዒ።] እ... አሁን መጽሐፍ ቅዱስን እዩትና ለውጦ የሚያውቅ ከሆነ መርምሩ። አይለውጠውም፡ ወዳጄ።

89 ሕዝቡን እንዴት አዘጋጀ? በመጀመሪያ፡ ምልክት ያለው ነቢይ ላከ፡ እርሱም ሙሴ ነው። ልክ ነው? [ጉባኤው “አሜን፡” አለ።—አርታዒ።] ምልክቱም “ተዘጋጁ፡” የሚል መልእክት ነበረው፡ ወደ ተሰፋይቱ ምድር ይወጡ ነበርና። በመቀጠል ይህ ነብይ፡ መለያ ነበረው፡ ያም በላዩ ላይ የነበረው ብርሃን ነው። የእሳት ዓምድ ይህን ነቢይ እንደተከተለው፡ ከሙሴ ጋር በምድረ በዳ እንደነበረ፡ እናውቃለን። ያንን አውቀናል። እና ከዚያ በኋላ መፍራት እንደሌለባቸው ለማረጋገጫ ምልክት ሰጣቸው፡ “ያንን ምልክት ሳየው፡ አልፋችኋለሁ፡” ባላቸው ጊዜ፥ ሁሉም ፈርተው ደንግጠው ነበር።

90 እንዴት እንዳደረገው ተመልከቱ። በመጀመሪያ ምልክትን፡ መልእክተኛን፡ የተለየ መልእክትን፡ የመልእክተኛውን መለያ፡ እና መንገዱ የተከፈለበት ስለመሆኑ የዋስትና ምልክት አዘጋጀ። ወደ ተሰፋይቱ ምድር እያመሩ ነው።

91 ዛሬም ያደረገው ተመሳሳይ ነገር ነው! ምን አደረገ? መንፈስ ቅዱስን ላከልን። መንፈስ ቅዱስ መልእክተኛ ነው፡ እና በቅዱሳት መጻህፍት ስለራሱ ማንነት በመካከላችን ይለየዋል፡ ይህም ትላንትና፡ ዛሬ፡ እና ለዘላለም ያው መሆኑ ነው። ምልክቱም ዋስትና ነው። የምንፈራው ምንድን ነው? ዋጋችን አስቀድሞ ተከፍሏል እናም ከመሥዋዕታችን ጋር የታወቁ ሆነናል። ታውቀናል። ቃል ገብቷል። ከቶም አይለቃችሁ።

92 አስቀድሜ እንደተናገርኩት፡ የእስራኤል ከግብጽ መውጣት፡ ሙሽራይቱ ከ—ከቤተ ክርስቲያን የመውጣቷ ተምሳሌት ነበር። ሙሴም አገልግሎቱን በጀመረ ጊዜ፡ እስራኤል ሁሉ በጌሤም ተሰበሰቡ፡ ጸሎትና አምልኮ ለማድረግ፡ በትክክል፡ ከግብጽ ምድር ሁሉ መጡ። ሙሽሪት የምትሠራው በዚህ መንገድ ነው፡ ከአሃዳውያን፡ ከሁለታውያን፡ ከሰላሴአውያን፡ እና ከሌሎች ሁሉ ትወጣለች። ትወጣለች። መሆንም አለበት። አሁን እዚህ በዕብራውያን ውስጥ ይህን እናነባለን... አሁን፡ ልናስብበት የሚገባው የመጀመሪያው ነገር፡ ከሁሉም ክፍሎች ውጡ፡ “ከአለማመን ከመካከላቸው ተለዩ።” እንግዲህ መንፈስ ቅዱስ በመጨረሻው ቀን “ከማያምኑት መካከል ከመካከላቸው ውጡ፡” በማለት እንደሚጠራ ቃል ገብቷል። ልብ በሉ።

93 በዕብራውያን 10:26 ላይ፡ እዚህ ጽፌዋለሁ፡ እንዲህ ይላል፡ “የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በኋላ ወደን ኃጢአት ብንሠራ፡ ከዚህ በኋላ ስለ ኃጢአት መሰዋዕት የለም፡” ወዳችሁ ብትክዱት ማለት ነው፡ እያችሁ።

94 አሁን እዚህ መናገር የፈለግኩት ነገር፡ ልብ ማለት ፈቃዳችሁ ከሆነ፡ ይህን ተምሣሌት ማሳየት እስክችል ድረስ ለአፍታ ታገሱኝ። በመንፈስ ይሰማኛል፡ በደንብ አልያዛችሁትም። እያችሁ? ልብ በሉ።

95 እነሆ ዕብራውያን፡ ጉዞው ላይ ነበሩ። እግዚአብሔርም፡ ተሻግረው ምድሪቱን ይሰልሉ ዘንድ፡ አሥራ ሁለት ሰው መረጠ፡ ማለቴ ሙሴ በእግዚአብሔር እጅ ይህን አደረገ፥ እና ተመልሰው ሲመጡ፡ የምድሪቱን ምልክት ይዘው መጡ። እዚያ በነበሩ ጊዜ ግን፡ አሰሮቹ እጅግ ፈሩ። “ለምን፡” “በዚያ የሚኖሩ አማሌቃውያን ናቸው፡ እኛም በፊታቸው እንደ አንበጣ እንመስላለን፡” አሉ። ኢያሱና ካሌብ ግን፡ “እንችላለን” በማለት፡ ማስረጃውን ይዘው ተመለሱ!

96 አያችሁ፡ የድንበር አማኞች ማለት እነዚያ ናቸው። በእነዚህ የተለያዩ ትእዛዛት፡ እና በቤተክርስቲያን፡ እና ቤተክርስቲያንን በመቀላቀል፡ እና ጥምቀቶች እና ትእዛዞች መጥተው ነበር። ይሁን እንጂ ምድሪቱ ህያው ስለመሆኗ ማረጋገጫ የሆነው፡ ያንን ህይወት… ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ ህያው መሆኑ፡ ምልክት ወደ መቀበል ሲሻገሩ ግን አልቻሉም። ያ ሌላ አድማስ ነው። እሱ በውስጥ ይኖራል። እሱ ከእኛ ጋራ ነው፡ አሁንም በውስጣችን አለ። ወደዚያ በደረሱ ጊዜ፡ “እረ፡” ሊያምኑ አልቻሉም። እጅግ ከበዳቸው፡ አያችሁ። ተመለሱም፡ ሁሉም፡ በምድረ በዳ፡ ሞቱ፡ ከእነርሱም አንድ ሰንኳ አልተሻገረም። እና፡ አስተውሉ፡ እኛም፡ ሜቶዲስቶች፡ ባፕቲስቶች፡ ፕሪስባይቴሪያን ካላመንን!

97 የድሮው አስተማሪዬ ዛሬ እዚህ ተቀምጧል ብዬ ተሰፋ አደርጋለሁ። ዶክተር ሮይ ኢ. ዴቪስ፡ ብዙዎቻችሁ፡ እዚሁ ፎርት ዋርዝ ውስጥ ታውቁታላችሁ፡ ምናልባት እዚህ ተቀምጦ ይሆናል። ከብዙ፡ እና ከብዙ አመታት በፊት፡ ስለነዚህ ነገሮች እንደተነጋገርን አስታውሳለሁ። በሚሰዮን ባፕቲስት ቤተክርስቲያን፡ በእምነት ያጠመቀኝ እርሱ ነው።

98 አሁን፡ ከቻላችሁ፡ ወደዚህ፡ ተመልከቱ… እ—እኛም ድንበር ድረስ ደርሰን፡ እንዲህ ብንል፡ “እንግዲህ፡ በልሳኖች እናገራለሁ፡ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን፡ ሃሌ ሉያ!” ይህ ብቻ አይደለም። ከቃሉ ውስጥ ይሄን አላምንም፡ ካላችሁ፡ በልምምዳችሁ ውስጥ የሆነ ችግር አለ። አያችሁ?

99 ወደ ምድሪቱ ድረስ ደርሳችሁ መኖሩን አይታችኋል። ኢየሱስ መነሣቱን አይታችኋል። በመካከላችን ነው። መልእክቱን ተከትሎ የሚመጣውን ቃል ሰምታችሁ፡ አሁንም ካላመናችሁ፡ ምን እንደሚሆን ታውቃላችሁ? እዚያው በምድረ በዳው ሞቱ። “የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በኋላ ወደን ኃጢአት ብንሠራ፡ ከእንግዲህ ስለ ኃጢአት መሥዋዕት አይቀርልንም።” የዕብራውያን መጽሐፍ የሚነግረን ይህንን ነው።

100 አሁንም፡ በምድር ላይ ያሉትን እሱ ቃል የገባቸው ታላላቅ የፍጻሜ-ዘመን ጠቋሚዎች፡ እያየን ነውና አስተውሉ፡ ጊዜው እንደቀረበ ምን ያህል ያስጠነቅቀናል። አለማመንን ተው። ተሰባሰቡ። እርስ በርሳችን እንዋደድ እንመንም፡ ራሳችንን ከዓለም መለየት አለብን።

101 አስተውሉ፡ ተሰብስበው ስለ መልእክቱ ብቻ ለመነጋገር አልመጡም። ወደ ውስጡ እንዲገቡ እንጂ፡ ከደሙ ስር ለመሆን። መጥተው እንዲህ ለማለት አይደለም፡ “ታውቃላልችሁ፡ ሙሴ እንዳለን፡ መልእክተኛው፡ እንዲህ ብሎናል፡ ደም እንድንቀባ ነግሮናል። ሰዎች ሆይ፡ ምን ታስባላችሁ? ” አይደለም። በጉን እረዱት፡ ደሙንም ቀቡት ነው!

102 ምልክት ሳይኖረን፡ መጥተን ተቀምጠን፡ ከቃሉ እና ከሌሎች ነገሮች ጋር መስማማት እንችላለን፡ ምን ይጠቅመናል? ጥቅም የለውም። ከሰሩ ተሸሸጉ። ከደሙ ስር ላልነበሩ ሁሉ ኃላፊነት አልወሰደምና። ዛሬም፡ ከምልክት ውጪ ለሚሆን ለማንም ሰው፡ ኃላፊነት አይወሰድም።

103 መላው ቤተሰብ፡ ምልክቱ ከተቀባ፡ እና ሁሉም ከምልክት ስር ሲቀመጡ ብቻ ደህንነታቸው ይጠበቃል። መላው ቤተሰብ! ይህን ታምናላችሁ? [ጉባኤው "ኣሜን፡" አለ።—አርታዒ።] ሰዎች ሆይ፡ ዛሬም ይሄን ማሰብ አለብን። ልጆቻችን ሆይ!

104 እናም ይህ የአፍላዎች-ዕድሜ ውስጥ የሚገኝ የማይረባ የሮክ-እና-ሮል፡ እና እኛ እያጋጠመን ያለን ነገሮች፡ እና እነዚህን ሁሉ ነፍሳት እና ትላትሎች፡ እና እነዚህ ሁሉ እዚህ በመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ተምሣሌት እንደሆኑ ታውቃላችሁን? በራዕይ ላይ ይናገራል። በእርግጠኝነት፡ ይናገራል። ሰለ ሰዎቹ፡ እ፡ እንደ—እንደ… እ፡ እ፡ እያችሁ፡ እ፡ እንዲህ አይደሉም… ሞተዋል። ሊነሱ አይችሉም። ዘላለማዊ አልነበሩም። በአሳቡ ውስጥ እንኳን አልነበሩም፡ ስለዚህ ይጠፋሉ። ለዘመናት ያበቃላቸዋል፡ ፈጽመው ይደመሰሳሉ። ለሠሩት ነገር፡ ለብዙ ዘመናት ይቀጣሉ፡ መጀመሪያ ያለው ማንኛውም ነገር መጨረሻ አለው።

105 መጨረሻ የማይኖረው፡ መጀመሪያ የሌለውን ነው። አንድ የዘላለም ሕይወት ብቻ አለ። አንድ አይነት የዘላለም ሕይወት አለ፡ እኛም ለዚያ እንጋደላለን። አስተውሉ።

106 ኢያሱ፡ የኢያሱ ምዕራፍ 2፡ ከአሕዛብ ወገን የነበረችው አማኟ ጋለሞታ፡ እና ቤተሰቧ፡ ከቀይ ገመድ ስር አወረዷቸው፡ እርሱም የኢያሱ መልእክተኞች ምልክት ነበረ። ገዳይ የነበረው የእግዚአብሔር መልአክ ያንን ምልክት አከበረው፡ በዚያች ከተማ፡ ያንን ብቻውን አከበረ። የእግዚአብሔር ብቸኛው፡ መስፈርት፡ እግዚአብሔር በአገልጋዮቹ ዘንድ፡ ይህን ምልክት እንደ መስፈርት ይፈልገዋል። የከተማው ከንቲባም ቢሆን፡ የከተማው ቅዱስ ሰው ይሁን፡ በከተማይቱ ባለው ትልቁ ቤተክርስትያን ውስጥ ቢገቡም አይገደኝም፡ ከዚያች ቤት በስተቀር በከተማው ያለው ሌላው ሁሉ ይጠፋል። እግዚአብሔር፡ ብቻውን፡ ያንን ምልክት አከበረ።

107 አስተውሉ፡ ኢያሪኮ እግዚአብሔር ታላቅ ነገር እያደረገ እንደሆነ ሰምታ ነበር፡ ነገር ግን ማስጠንቀቂያውን አልተገነዘቡትም።

108 ዛሬም ሰዎች እግዚአብሔር ላለፉት ጥቂት ዓመታት ሲያደርግ የነበረውን እየሰሙ ነው፡ ይሁን እንጂ አይገነዘቡትም። ይህ ታላቅ የጸጋ እና የምልክቶች ኃይል፡ "በሰዶም ዘመን እንደ ሆነ፡ እንዲሁ ይሆናል፡" በላት ቃል ገብቷል። ያ ነገር እንዴት እንደሚሆን ቃል ገባ! በሰዶም የተከሰተውን ተመልከቱ። የሰዶም ምልክት እንዳለ፡ አሰቡ። የሚልክያስ 4፡ መልእክተኛ ግን፡ "የህዝቡን ልብ ወደ አባቶች መመለስ፡ የጴንጤቆስጤ አባቶች፡ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መመለስ ነው።" ሌላ መጽሐፍ ቅዱስ፡ ሊኖር አይችልም። ሙሉው የእግዚአብሔር መገለጥ ይህ ነው።

109 እና አንዳንዶች "እንግዲህ፡ እኔ በከፊል **ይሄን** አምናለሁ፡ ስለዚያ ግን አላውቅም፡" ይሏችኋል።

110 እውነተኛው የእግዚአብሄር መልእክተኛ ወደ ሙላት ይመልሳችኋል! አያችሁ? ልብ በሉ፡ መንፈስ ቅዱስ የሚያደርገው ያ ነው፡ ወደ እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ቃል ይመልሳችኋል።

111 ጸጋው ታይቷል፡ ከዚያ በመቀጠል ፍርዱ ነበር። በታላላቅ ቤተ እምነት ህንፃዎቻቸው ውስጥ ደህና እንደሆኑ አምነው ነበር እያሪኮአቸው ነበረላቸውና፡ ይሁን እንጂ እንደማይጠቅም ተረዱ።

112 መቼም አንዳች ነገር ሳይኖር አይቀርም... ብቻ በሆነ መንገድ ወደዚያ የደረሱ፡ ወደዚያ የደረሱ ሁለት ወጣቶች ነበሩ፡ ገብተውም አስቀድሞ የተወሰኑትን ዘር ሁሉ አንድ ላይ እንዲሰበሰቡ ነገሯቸው። እሷም... ቤቷን ለቤተ ክርስቲያን ተጠቀመች፡ መልእክተኞቹንም ተቀበለቻቸው፥ ከዚያም በከተማዋ የሚኖሩትን፡ ከምልክት ስር ለመሆን፡ ያመኑትን በሙሉ ሰበሰበች።

113 ከዚህ ታላቅ ከተማ ውስጥ አንዲት ሴት ብቻ! ያውም የተበላሸ ስም የነበራት፡ ምስኪን ሴት፡ ምናልባት በከተማው ውስጥ ካሉት ቤተክርስቲያን ሁሉ የተወገዘች ትሆናለች፡ መልእክተኛውን ግን አመነች። መልእክተኛውም ምልክቱ ተወላት፡ ምልክት፡ እግዚ አብሔርም ምልክቱን አከበረው። ዛሬም እንደዚሁ ነው። ያንን እጥፊ የእግዚአብሔር ቁጣ በመጣ ጊዜ፡ ያንን ታላቅ ሰርዓት በወደቀ ጊዜ፡ ምልክቱ ቤቷን እንደ ጠበቀ፡ አስታውሱ። እምነት ስለነበራት እና ምልክቱን ተግባራዊ ስላደረገች እንጂ፥ እሷ ጥሩ ሴት ስለነበረች አይደለም።

114 እስኪ አሁን እንዲህ ብትል ኖሮስ፡ "አዎን፡ እነዚህ ሰዎች ጥሩ ሰዎች ናቸው፡ በተናገሩት መልእክት ተባርኬበታለሁ፡ ይሁን እንጂ፡ እውነቱን ለመናገር፡ ያ ገመድ በመስኮቴ ላይ እንዲንጠለጠል ማድረግ መሞኘት ነው፡ በቃ ወደ ውስጥ ልሳበው" ብትልስ? ይፈርስ ነበር። ይፈርስ ነበር። በግብጽ እንደነበረው የሕይወት ምልክት፡ እግዚአብሔር ምልክቱን ብቻ ያከብራል።

115 ኢያሱ የኢየሱስ ምሳሌ ነበር፡ ምክንያቱም **ኢያሱ** ማለት "ያህዌህ-አዳኝ" ማለት ነው። እሱ የኢየሱስ ተምሣሌት ነበር፡ መልእክተኛው ለሰበከው ለምልክቱ ምልክት ታማኝ ነበር። ኢያሱ ለዚያ ለምልክቱ ምልክት የታመነ ነበር። በግብጽ ውስጥ፡ ከዚያም በታች የነበሩት ሁሉ ድነዋል። በኢያሪኮ ውስጥም፡ ከዚያ በታች የነበሩት ሁሉ ድነዋል።

116 ዛሬም የበጉ ደም የምልክቱ ተምሣሌት ነው፡ ይህም የዛሬ ምልክት መንፈስ ቅዱስ መሆኑ ነው። በሰሩ የሚሆን ሁሉ ደህንነቱ የተጠበቀ ነው። ከሰሩ ውጪ የሆኑ ሁሉ ደህንነታቸው የተጠበቁ አይደሉም። በዕብራውያን 13፡10 እና 20 ላይ "የዘላለም ኪዳን፡" ተብሎ ተጠርቷል። ብሉይ ኪዳን አንድ ነገር ነው፡ ይሄኛው አዲስ ነው፡ ይህም "የዘለአለም ኪዳን" ነው።

117 እግዚአብሔር፡ በደም-ባጸናው ቃል ኪዳን፡ ከሐጢአት እና ከውርዴት፡ እና ከሌላው ዓለም ሁሉ ነጻ ያደርገናል። የተለየ ልብስ መልበስ አይጠበቅባችሁም፡ ማንም ሰው የተለየ ልብስ መልበስ ይችላልና። በውስጣችሁ፡ የተለያችሁ፡ መሆን አለባችሁ። ሕይወት ከውስጥ ነው፥ መልበስም፡ አለመልበስም አይደለም። "የእግዚአብሔር መንግሥት መብልና መጠጥ፡ ወይም ልብስ መልበስ አይደለችምና፥ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ የሆነ፡ ጽናት፡ በጎነት፡ ጨዋነት፡ ትዕግስት ሁሉ ነው።"

118 አሁን፡ ተሰፋ ቃላቶቹ ከሐጢአት ነጻ ያደርጋሉ፡ ይህም እግዚአብሔር ሐጢአታችሁን እ—እንዳላሰበ የሚያስረዳ ነው። ዳዊትም “እግዚአብሔር ኃጢአቱ የማይቆጥርበት ሰው የተባረከ ነው፡” ብሏል። ስለዚህ እግዚአብሔር በዚያ ምልክት ላይ ኃጢአትን በፍፁም አይቆጥርም፡ ምክንያቱም ምልክቱ እግዚአብሔር አስቀድሞ የተቀበለው የተከፈለበት ምልክት ነውና። ለዚያም፡ ምልክት ይዛችኋል-... ይህም በእምነታችሁ የተገዛ ነው። ስለዚህ እሱን ለማምለክ እና ኃይሉን እና ተሰፋ ቃሉን ለማሳየት፡ ስለ ቤዛነታችሁ የተከፈለው ዋጋ በሰውነታችሁ ውስጥ አለ።

119 **አዲስ ኪዳን** ማለት “አዲስ ቃል ኪዳን” ማለት ነው። **ደም** ማለት “ህይወት” ማለት ነው። አዲስ ኪዳን የመንፈስ ቅዱስ ኪዳን ነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስን ከሙታን ያስነሣ እርሱ ኢየሱስ ለእኛ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ሁሉ እንዳሟላና፡ ዛሬም ሕያው መሆኑን ያሳየበት፡ የመንፈስ ቅዱስ ምስክር ነው። ምልክቱም እርሱ በገባው ቃል መሰረት ከኛ ጋር እራሱን ለመለየት፡ ህያው መሆኑን ያረጋግጣል። አሁን አንድ ሰው እንዴት መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ ቃል እንደገባለትና፡ ክርስቶስ በእነዚህ የመጨረሻ ቀናት በመንፈስ ቅዱስ አምሳል መመለሱን እና እራሱን ህያው አድርጎ መግለጹን እንዴት ማየት ይችላል? ። ያ በምልክት ነው። በምልክቱ ነው። በተከፈለው ዋጋ ያ ነው።

120 በሆነ ስሜት ላይ በጭራሽ አትታመኑ። “ጀርባዬ ላይ ቀዝቀዝ ያለ ነገር ተሰማኝ። እ—እ የ—የሆነ ነገር ሸተተኝ፥ በእጄ ላይ ደም አየሁ፡” ወይም ዘይት አየሁ። ወ—ወይም፡ “የባችለር ዲግሪዬን ተቀበልኩ።” ወይም፡ “በመንፈስ አሸበሸብኩ። ጮህኩ። በልሳኖች ተናገርኩ።” እነዚህ ነገሮች ደህና ሊሆኑ ይችላሉ። እኔም ተቃውሞ የለብኝም፡ እኔ የማወራው ነገር ግን ያ አይደለም።

121 እኔ የማወራው ግን የምልክቱ መታወቂያችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከሙታን ተነስቶ በእኛ ውስጥ ስለ መሆኑ፡ ራሱን በመለየት፡ የገባልንን የዚህን ዘመን ቃል እንደገና-ለማረጋገጥ መምጣቱ ነው። ኣሜን። ያን ጊዜ እናንተ እና ክርስቶስ አንድ ናችሁ። እግዚአብሔር እና ክርስቶስ አንድ ናቸው። “እኔ በአብ እንዳለሁ፡ አብም በእኔ እንዳለ፥ እኔ በእናንተ፡ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ፡ በዚያ ቀን ታውቃላችሁ።” ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላ፡ ሕያው ሆኖ እራሱን በሰው ሥጋ ያሳየ፡ እግዚአብሔር አለ። ምልክት ይኸው ነው።

122 ወዳጆች ሆይ፡ ገና ያልገባችሁ ከሆናችሁ፡ ፈጥናችሁ ግቡ። ፈጽሞ ረፍዶ ሊሆን ይችላል። እኛ አናውቅም።

123 መገኘቱን፡ አዲስ ኪዳንን፡ ደሙን አሳይቷል። አሁንም ህያው ነው፡ ማረጋገጫዎችን እያደረገ ይገኛል። እርሱ ህያው ስለሆነም፡ እርሱ ለገዛልን ነገሮች ሁሉ ባለ መብት ነን። የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ያገኘ ሰው፡ ወይም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን ያገኘች ሴት፡ ኢየሱስ ለእኛ ስለገዛልን ነገሮች ሁሉ ባለ መብት ናቸው፡ የተቀበልነው ምልክት እርሱ ነውና። የመግዛት ኃይልም እርሱ ነው።

124 ለምሳሌ እንዲህ በሉ፡ “እሺ፡ ወንድም ብራንሃም፡ ምን ማለትህ ነው? ”

125 እዚህ ጋር፡ ግልጽ ላድርገው አሁን፡ እናንተ የታመማችሁ ሰዎች ይሄን በደንብ ስሙት። ይኸውላችሁ፡ በጣም ተርቤ እና አንድ ዳቦ አለ፡ የዳቦው እሩብ ዋጋው፡ ሃያ አምስት ሣንቲም ነው፡ እንበል፡ እና አንድ ወንድም መጥቶ፡ “ይኸው

ሃያ አምስት ሳንቲም፡ ወንድም ብራንሃም። በጣም ተርበሃል፡ ይኸው ሃያ አምስት ሳንቲሙን እንካ።" አሁን፡ በእጄ በያዝኩት ሃያ አምስት ሳንቲም ዳቦው በእጄ የያዝኩትን ያህል ደስተኛ እንደሚያደርገኝ፡ ይህን ታውቃላችሁ፡ ምክንያቱም የመግዣውን ዋጋ ይዣለሁ። ዳቦውን የምገዛበት ምልክት ይዣለሁ። ዳቦውም አጠገቤ አለ፥ እኔ የያዝኩት ግን፡ ዳቦውን የምገዛበት ሃያ አምስት ሳንቲም፡ ማለት ምልክት ብቻ ነው፡ በዳቦው መደሰት የምችለውን ያህል በምልክቱ ደስተኛ መሆን እችላለሁ።

126 አሁን፡ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ከተጠመቃችሁ፡ ይህም ኢየሱስ የሞተለትን የቤዛነት ነገሮች በሙሉ የእናንተ ስለመሆናቸው ይህ ምልክት ነው፡ የእናንተ ነው፡ በእጃችሁ ውስጥ ገብቷል። ይገባኛል ለማለት ትፈራላችሁን?

127 ኪሴ ውስጥ ካስገባሁ፡ እና "እንጃ፡ ያንን ዳቦ መግዛት እችላለሁ ወይስ አልችልም አላውቅም፡" ካልኩኝ፡ በረሃብ እሞታለሁ። ነገር ግን አስታውሱ፡ ነጋዴው እንዲህ ይላል፡ "ሚስተር ብራንሃም ሆይ፡ መስፈርቴ አንድ ናት። ሃያ-አምስት ሣንቲም ብቻ ናት፡ በዚያች ዳቦውን መግዛት ትችላለህ።" ተቀብያለሁ! አሜን። ይኸው ነው።

128 ዛሬ ብዙ ነገሮች ሲፈጸሙ የማናየው ለዚህ ነው፡ ምልክት፡ እውነተኛውን ምልክት ስላልተቀባ ነው። አዎን፡ ሁሉም አይነት ፎርጂዶች አሉን፡ እኔ የምለው ግን ትክክለኛውን ምልክት ነው።

129 ተመልከቱ፡ ይሄን ተገንዝበን ምልክቱን ስናቀርብ፡ ስለ ምልክቱ የተቀባ ህይወት፡ ማለት ደሙ ራሱ ይናገርልናል። አስታውሱ፡ የቃል ኪዳኑ ደም ከምልክቱ ጋር የታወቀ ነው፡ ቃሉም የተሰፋውን ኪዳን ያረጋግጥልናል። ምልክቱ ስለ እኛ የተገዛ ግዢ መፈጸሙን የሚያሳይ ምልክት ነው።

130 አሁን፡ በዚያ ውስጥ ካልተካተታችሁ፡ መቼም፡ እርግጥ ነው፡ አንዳች አታገኙም፥ የጸሎት መስመር አልፋችሁ እንደመጣችሁ፡ ተመልሳችሁ ትወጣላችሁ፥ ወደ መሰውያው ትወጣላችሁ፡ ዙርያውን አይታችሁ፡ ትወጣላችሁ።

131 ገር ግን፡ ወንድሜ ሆይ፡ ምልክቱ፡ አንዴ በ—በ—በልብህ ውስጥ ከተደረገልህ፡ እና በውስጥህ ያለው የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ እንደሆነ ካወቅህ፡ የሆነ ነገር እየተፈጠረ ነው። ማንም አያስቆምህም። የማን እንደሆንክ አንተ ራስህ ታውቀዋለህና። ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ቃል መታዘዝ ምልክት የማግኘት መብት ያስጥሃል፡ በሌላ አይደለም። "ትእዛዙን ሁሉ የሚጠብቅ ብጹእ ነው፡ ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስ መብት ይኖረዋልና።"

132 ከዚያ በኋላ፡ ስንጸልይ፡ ከጸሎታችን ጋር ምልክቱን ይዘን መቅረብ አለብን። እንግዲህ ይሄን ሳትረዱት እንዳያልፋችሁ። በምትጸልይበት ጊዜ፡ ጸሎታችሁን የምታጸኑበት ምልክት ያስፈልጋችኋል፥ ካልሆነ ግን፡ ምልክቱ እስኪመጣላችሁ ድረስ ጸሎታችሁን ቀጥሉ፡ ምክንያቱም ትቀበሉት ዘንድ ተስፋ ቃል የላችሁምና። እያችሁ፡ በመጀመሪያ ምልክቱ ይኑራችሁ፥ የክፊያው ዋጋ እርሱ ነውና፡ ያንን ለማመን እምነት ይኑራችሁ።

133 ይህም፡ ሙሉ በሙሉ የመታዘዝ ማሳያ ነው። ፍርሃት ሁሉ ተወግዷል። ጳውሎስ እንዲህ ይለናል፡ "ደሙ በተሻለ መልኩ ይናገራልና።"

“ደሙ ይናገራል፡” ነው ያልከው? አዎን፡ ደሙ ይናገራል።

134 በዘፍጥረት 4:10 ላይ፡ እግዚአብሔር—የቃየን... ወይም “የአቤል ደም ከምድር ይናገራል፡” ሲል እናያለን። በዕብራውያን 12 ላይም፡ “የክርስቶስ የቃል ኪዳን ደም ከአቤልም ደም ይልቅ የሚሻል ይናገራል፡” ይላል። አያችሁ? ደሙ እንደሚናገር ተረድተናል፡ ስለ እናንተ ይናገራል። በእናንተ ውስጥ ያለው ህይወት ከፈሰሰው ደም ይናገራል። አሜን። ኦህ፡ ወንድሜ! ሁሉም ሰው ይህን ቢያየው እመኛለሁ። አያችሁ? ምን እንደሆነ ካያችሁ፡ በእናንተ ዘንድ ያለው ህይወት ነው። አያችሁ፡ እናንተን ከሱ ጋራ እንድትታወቁ የሚያደርጋችሁ ያ ደም ነው። ያ ምልክት ነው። ያ... ምንድነው፡ ደሙ ስለ እናንተ ፈሰሰ፥ እናንተም ተቀበላችሁት፡ ህይወቱም ወደ እናንተ መጣ። ያን ጊዜ ምልክቱ ተቀበላችሁ፡ እሱም መንፈስ ቅዱስ ነው።

135 ስለዚህ በምንጸልይበት ጊዜ፡ እንዳልኩት፡ ከጸሎታችን ጋር ለማቅረብ ምልክት ሊኖረን ይገባል፡ አሁንም በግብጽ እንደነበረ፡ በኢያሪኮም እንደነበረ፡ ወይም በሐዋሪያት ሥራ 16:31 እንደሆነ፡ ስለራሳችን እንመንና ምልክቱን መላውን ቤተሰባችን እንቀባ። ጳውሎስ ለሮማዊው መቶ አለቃ፡ “አንተ እመንና፡ ቤተሰብህም በሙሉ ይድናሉ፡” ብሎታል። ለቤተሰብህ ሁሉ ተጠቀምበት። ያልዳነ ልጅ ካለህ፡ ምልክቱን በላዩ ላይ ጫነው፡ እና “ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡ እሱንም ዋጀሁት፡” በል። በዚያው ጽና። የጠፉች እናት ወይም ወዳጆች ካሉህ፡ ምልክቱ ጫንባቸውና፡ “ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡ ዋጀኋቸው፡” በል።

136 ከዓለማዊው ቆሻሻ ሁሉ፡ ውጣ፡ ከቤትህ አስወግድና፡ ለእሱ ዝግጁ ሁን። ቁምጣዋችህ አስወግድ። ካርታዎች ከጠሬጴዛህ አስወግድ። ሲጋራዎችን አስወግዳቸው። አለማመንህን እና የቤተክርስትያን ወረቀቶችህን፡ ወደ ስፍራቸው ጣላቸው። ኣሜን። ያኔ ዝግጁ ትሆናንለህ። ከዚያስ ምን ላድርግ? ከዚያማ ምልክቱን በጸሎትህ ላይ አቅርብ፡ ከትክክለኛ ማረጋገጫ፡ ከትክክለኛ እምነት ጋር አቅርበው። ተጠቀምበት፡ በሙሉ ድፍረት ተጠቀምበት። ምልክቱን ስትጠቀምበት፡ አሁን በደንብ የጸዳህ ትሆናለህ። “ልባችን ካልፈረደብን፡ ልመናችንን እናገኛለን።”

137 እናንተ ሰዎች የተሳሳተ ነገር እያደረጋችሁ እስከሆነ ድረስ፡ ስህተት እንደሆናችሁ እያወቃችሁ እግዚአብሔር አንድ ነገር እንዲያደርግላችሁ እንዴት ትጠይቁታላችሁ? ወደ ኋላ እና ወደ ፊት የምፍገመው ምክንያቱ ይህ ነው። ይህን የምለው እናንተን ለመጉዳት አይደለም። ይህን የምለው ለማስተካከል፡ ነገሮችን ትክክል ለማድረግ ነው። በሰዶምና በገሞራ ፍርስራሽ ላይ ሆናችሁ ይህን ማድረግ እንዴት ትችላላችሁ? ተመለሱ!

138 ማኅበራት እና አገልጋዮች ህዝቡ ማንኛውንም ነገር እንዲያደርጉ፡ እንዲቀጥሉበትም ፈቅደውላቸዋል፡ ስሞቻቸውን በመጽሐፋቸው ያስመዘግባሉ ከዚያ በኋላ እርኩሰት የሆነውን ነገር ላይ **እንዲህ፡ እንዲያ፡** እና **ሌላ፡** ይሏቸዋል። እናም እምነት ያልሆነ ነገር እንዲሆን ተደርጓል... ይህ ምን እንደሆነ በጥቂቱ እንኳ አያውቁትም። ተስፋ፡ ይኖራቸዋል፡ እምነት ግን አይኖራቸውም።

139 ሁሉም ነገር፡ በደንብ ተበጥሮ የጸዳ ስለሆነ፡ መመለስ አለባችሁ። ከዚያ በኋላ ኢየሱስ ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ስለመሆኑ እወቁና፡ ምልክታችሁን

እንሆ፡ ተጠቀሙበት። የሆነ ነገር ካልተፈጸመ፡ ችግር አለ፥ እንደገና ተመለሱ፡ ስሕተቱን በእጅህ ያዝ። ቃል የገባው እርሱ ነው። ቃል ኪዳን ያደረገው እርሱ ነበር። ተጠቀሙበት። ኤፌሶን 2:12 አንብቡ፡ አንዳንድ ጊዜ፡ ከ— ከፈለጋችሁት፡ እዚያው ታገኙታላችሁ።

140 በዕብራውያን 9:11 ላይም፡ እስተውሉ። ጳውሎስ እንዲህ አለ፡ "ሕያው እግዚአብሔርን፡ በሕያዋን ቃሎች አገልግሉ።" ልክ ዕብራዊ እንደሚያደርገው አይደለም፡ መስዋዕቱንም ተሸክሜ፡ በመንገድ ላይ እወርዳለሁ፡ ትልቅ የሰባ ወይፈን ተሸክሜ እገባለሁ፡ ከዚያ በኋላ እጆቹን ይጭንበታል፡ ከዚያ ደሙን ያፈሳል፡ ጸድቆ ይመለሳል። የያሕዌህ መስፈርት ነበረ። ያደርጋል። ከዚያም ቀጣዩ ትውልድ፡ ምናልባት እነርሱ ትንሽ ቀዝቀዝ ይላሉ፡ ትንሽ ቀዝ ቀዝ ያለ፡ ሌላ ሰው። በመጀመሪያ የሚሆነው ነገር፡ የቤተሰብ ባህል ይሆንባቸዋል።

141 ለእኛም ጴንጤቆስጤ የሆነብን ይህ ነው፡ የቤተሰብ ባህል ሆነብን። ወጥተን፡ እንዲህ እንላለን፡ "ዛሬ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ድንቅ ነበር አይደል? በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተደረገው ነገር አይደንቅም ወይ? ጌታ ኢየሱስ፡ ፈወሰ... " አቤቱ፡ ማረን! አያችሁ? የቤተሰብ ባህል-... "ታውቃለህ፡ በቀደም'ኮ በልሳን ተናገርኩ። ታውቃለህ፡ እኔ **የዚህ፡** ወይም **የዚያ** አባል ነኝ። ኧሃ-ሃህ።" ኦህ፡ የቤተሰብ ባህል ነው!

142 እግዚአብሔር የተናገረውን ታውቃላችሁን? እግዚአብሔር እንዲህ አለ፡ "ሰባችሁ እና በጎቻችሁ በአፍንጫዬ ግማት ናቸው። ልክ ነው፡ መስዋዕታችሁ ገምቷል።"

143 የጴንጤቆስጤ መስዋዕቶችም እንዲሁ ሆኗል፡ የቤተ እምነት ሰልታ-ሰልቶች እና ብልጣ-ብልጥነት፡ ሴቶቻችንም ወንድሞቻችንም የሚያደርጉት ሁሉ፡ የአምልኮት መልክ አለው፥ ሙዚቃውን በደንብ ይከውኑታል፡ አንዱም ለአፍታ ያህል ወደ ላይ-ወደ ታች ይዘላል፥ ከዚያ ያበቃል፡ የእግዚአብሔር ቃል በሆነ መንገድ ከመጣና ከተነገረ ግን፡ ባልዲ ሙሉ ውኃ እንደተቸለሰበት ሰው ይሆናሉ። ችግሩ ምንድነው? መሥዋዕታችሁ በያሕዌ ፊት መግማት ጀመረ።

144 በዚያን ጊዜ ነበር ኢሳያስ ወደ ሰፍራው የመጣው፡ እርሱም እንዲህ አላቸው፡ "እነሆ ዘለአለማዊ ምልክት እሰጣችኋለሁ፡ ድንግል ትጸንሳለች።" አያችሁ፡ ይኸውላችሁ። በሥራ ቅርጾች እና በሐይማኖት መግለጫዎች፡ ሳይሆን፥ በሕያው ቃላት፡ ከሙታን መካከል ተነስቶ፡ በመካከላችን በሚኖረው ሕያው አምላክ።

145 በእንደዚህ ነገሮች የሚያምኑ፡ አንዳንዶቹ፡ እነዚህ አብያተ ክርስቲያኖች፡ ምልክት የሚባል ነገር የለም በማለት ይክዳሉ። እና፡ አንድ ወዳጄ እንዲህ ሊለኝ ሞከረ፡ "መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉት አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ብቻ ናቸው። ያ ብቻ ነው። አዎን።" ኦህ!

146 እኛ ቃሉን የምናምን ግን፡ ከዚህ የተለየ እናውቃለን፡ ይህ ነገር ሕያው መገኘቱ እንደሆነ እናውቃለን። በመካከላችን ያለው መንፈስ፡ ሕያው የክርስቶስ መገኘት መሆኑን እንዴት እናውቃለን? እሱ ያደረጋቸው ተመሳሳይ ነገርር ስለሚያደርግ። ማስረጃው ይህ ነው። ወይን የሚታወቀው በሚያፈራው ፍሬ ነውና። እንግዲያውስ ፊተኛው የወይን ግንድ ወጥቶ ከኋላው የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ከጻፉበት፡ እና ኢየሱስ ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር፡ ሐዋርያትም

ካደረጉ፡ እንግዲያውስ ያ ወይን ዳግመኛ ከመጣ፡ አሁንም ተመሳሳይ ነገር ያደርጋል። ዕብራውያን 13፡8 ተመልከቱ፡ እሱ ያው ነው ይለዋልና፡ ኦህ፡ ማይ፡ እግዚአብሔር እንደ ተስፋ ቃሉ፡ ለእኛ እንዳስነሳው ያረጋግጣል። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]

147 የቃል ኪዳን ማህተም! ኤፌሶን 4፡30 እንዲህ ይላል፡ "እስከ ቤዛችሁ ቀን ድረስ የታተማችሁበትን፡ ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ።" እስከሚቀጥለው ሪቫይቫል ድረስ አላለም። "እስከ ቤዛችሁ ቀን ድረስ!" እንደ አንደኛ ቆሮንቶስ 12 መሰረት፡ ወደ እርሱ ስለተጠመቅን። በእርሱም ሙላቱ አለ፡ ኃጢአትም በእርሱ ዘንድ አይታወቅም። "ከእግዚአብሔር የተወለደ ኃጢአትን አያደርግም። የእግዚአብሔር ዘር በእርሱ ይኖራል፡ ኃጢአትንም አይሠራም።" ምልክት እያለበት፡ እንዴት ይሰራል? ይህ ምልክት ተቀባይነት ስለማግኘቱ ማሳያው ነው።

148 እና፡ እንግዲህ፡ "ኃጢአት ሠርቻለሁ፡" የምትሉ ከሆናችሁ። እንግዲያውስ፡ ምልክቱን ፈጽማችሁ አልተቀበላችሁም። አያችሁ?

149 ምልክቱ አጥር ነው፡ ዋጋ መከፈሉን ያሳያል። ሰይጣን ይሄን ሊሰጣችሁ ሲሞክር... ይህን አስቡ። ሰይጣን ሕመም ሊሰጣችሁ ቢሞክር፡ ወይም የሆነ ነገር ሊሰጣችሁ ቢሞክር፡ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ታውቃላችሁ? ምልክታችሁን አሳዩት። እውነት ነው፡ ክርስቲያን ሊታመም ይችላል። ምልክትህን አሳየው፡ በዋጋ የተገዛህ የእግዚአብሔር ምርት መሆንህን አረጋግጥለት። "ዲያብሎስን ተቃወሙት፡ ከእናንተም ይሸሻል።" በተስፋ ቃሉ ላይ በማይወዛወዝ እምነትህ ላይ ምልክቱን ያዝ።

150 እግዚአብሔር በአንድ ወቅት ለማሳያ የቀሰተ ደመና ምልክትን ሰጠ። እየጨረሰኩ ነው። ለማሳያ የቀሰተ ደመና ምልክት ሰጠ። አሁን አሥር ደቂቃ ያህል አለኝ፡ ከዚያ የጸሎት መሰመር ይኖረናል። ለዚያ ምልክት ታማኝ ሆኖ ጸና። አይደል? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] አሁንም ይጸናል። በእነዚህ ሺ አመታት ውስጥ፡ አንድም ቀን፡ አንድም ጊዜ፡ ሳያሳይ ቀርቶ አያውቅም። ስለ ምልክቱ ታማኝ ሆነ፡ ምልክቶቹን ፈጽሞ... አለማክበር እንደማይቻለው አሳየን። ምንም ቢሆን ግድ የለኝም...

151 ኢየሱስ ለአሥር ሺሕ ዓመታት ባይመጣም፡ ምልክት ከያዛችሁ፡ የማክበር ግዴታ አለበት። ምንም ያህል ነገሮች ቢቀየሩ፡ እና ምንም ይሁን ምን፡ ያንን ምልክት ማክበር አለበት። እሱ ራሱ እንደሚያከብር ተናግሯል። በጣም ጥሩ። እግዚአብሔር-በሰጠን እምነት ላይ የእርሱን ምልክት፡ በአገር አቀፍና፡ በአለም አቀፍ ደረጃ ላሉ እምነት አልባ ለሆኑ ሁሉ፡ አማኞችን ምልክቶች እና ድንቆች አይከተሏቸውም ብለው ለሚያምኑ አሁን እንድናሳይ ይጠብቅብናል። እናንተም ለምልክቱ ታማኞች ሁኑ፡ ይህም ዋጋው እንደተከፈለ እና እኛም ለትንሳኤው እንደተቀበልነው፡ የሕይወትን ምልክት በውስጣችን እንዳለን ያሳያል።

152 ከባድ መልእክት ነው፡ ግን እውነት ነው። እኛ የምንፈልገው፡ እውነት ነው። እውነትን እንድናውቅ እግዚአብሔር ይርዳን። "እውነትን ታውቃላችሁ፡ እውነትም አርነት ያወጣችኋል።" ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለምም ያው ነው እላለሁ። አሁንም ሙሽራይቱ ከቤተክርስቲያን ከመሄዷ

በፊት፡ ከዘጸአቷ በፊት፡ እግዚአብሔር አሁንም፡ መ—መንፈስ ቅዱስን እንደ ምልክት እንደሚሰጥ አምናለሁ።

153 ብዙ አሸንክታቦች እንዳሉ፡ እና ሰዎች እንጮኻለን፡ ልሳን እንናገራለን እንደሚሉ አምናለሁ። እኔም ብሆን በእነዚያ ነገሮች አምናለሁ፥ ቢሆንም ግን በዚያ ላይ መተማመን አትችሉም። በዛ ላይ ተማምናችሁ፡ ቃሉን እንዴት ትክዳላችሁ? አያችሁ?

154 ምልክት እራሱን በውስጣችሁ በመለየት፡ በራሱ የሚኖር በእናንተ ዘንድ ያለው ቃል ነው። እግዚአብሔር የራሱ ተርጓሚ ነው ማለት ይህ ነው። "እንግዲህ፡ አሁን፡ ልሳኔን ተርጉምልኝ፡" ማለት አይጠበቅባችሁም። ያ አይደለም። እሱ ራሱ ህይወታችሁን በቃሉ ይተረጉመዋል። ማንነታችሁ የሆነውን፡ ቃላችሁን ይወስድና፡ የገዛ ቃሉን በዚያ ይለያል፡ ምንም ትርጓሜ አያስፈልግም፡ ያለ ነገር ነው። እግዚአብሔር የራሱን ትርጓሜ ሰርቷል፡ እኛም የዘመኑ እነዚህን ተስፋዎች ተቀብለናል።

155 ዳላስ ሆይ፡ እናንተ የተወደዳችሁ የክርስቲያኖች ቤተሰቦች፡ ዛሬ፡ በዙርያችሁ በምትመለከቱት፡ በዚህ ነገር አትወሰዱ፡ ጠፊ ነውና። ምልክቱን ዘወትር ተጠቀሙበት፡ ምልክቱን ቀቡት። መጽሐፍ ቅዱስን አንብቡት። ወደ ሁሉም ነገር ቅረቡ። እና በውስጣችሁ ያለው መንፈስህ "ኣሜን" ካላለ፡ ያን ጊዜ ወደ ኋላ መመለስ ይሻላችኋል፡ የያዛችሁትን ነገር፡ በምልክቱ ቀይሩት፥ ገና አላገኛችሁትምና።

156 በአንዲት የከሰዓት ክፍለ ጊዜ ውስጥ ይህ ሁሉ መናገር አይቻልም። አሁንም አራት-ከሰላሳ ሆኗል። ሰዓቱ አልቋል፡ እስከነ ጸሎት መሰመሩ ጋር አምስት ሰዓት ድረስ ከጨረስን በቂ ነው።

157 ኢየሱስ ክርስቶስ ዛሬ እንደሚኖር እና እንደነገሰ ታምናላችሁን? [ጉባኤው "ኣሜን፡" አለ።—አርታዒ።] የነገርኳችሁ ነገር እውነት ነው ብላችሁ ታምናላችሁ? ["አሜን።"] መስፈርቱ፡ ምልክት ነው። እኔ እውነት የሆነውን ብቻ እናገራለሁ። የማየውን፡ የምሰማውን፡ የተገለጠልኝን ብቻ እናገራለሁ። ይህን ለምን እላለሁ፡ ከአስር ሺህ ጊዜ በሺዎች የሚቆጠሩ ጊዜ፡ አንድም ቀን ተሳስቶ አያውቅም፡ ያም እግዚአብሔር መሆን አለበት። እግዚአብሔር መሆን አለበት። እሺ፡ የሚናገረውን ለማያውቅ ሰው እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን አገልግሎት ይሰጠዋልን? ["በጭራሽ።"] በአንድ ወቅት ነብይ እንዲሆን የለየውን ሰው፡ በሌላ ጊዜ የተደባለቀ-ቃል ይሰጠዋልን? ["በጭራሽ።"] የተደባለቀበት፡ ለሚክደው ነው። እግዚአብሔር አይደባለቅበትም። እግዚአብሔር የራሱ ተርጓሚ ነው።

158 ምልክቱን ተቀበል! ወደ የትኛውም ቤተ ክርስቲያን ወይም ማንኛውንም ዓይነት፡ ወይም ማንኛውንም ነገር በመቀላቀል ላይ አትረፍ። ምልክቱም ይኑርህ! አጥብቀህ ያዘው። እግዚአብሔር የሚያውቀው ብቸኛው ነገር እሱን ነው። ወደዚያች ሰዓት በተቃረብህ ጊዜ፡ ሞትህ ሲመጣ፡ ያንን ምልክት በራስህ ላይ ብትይዝ ይሻልሃል፥ እርሱ በሚመጣበት ቀን፡ በትንሳኤው፡ ያንን ምልክት ማቅረብ እንደምችል እውቃለሁ። በዚህ አካል ውስጥ አይሆንም፡ የበሰበሰ ነውና፥ ነገር ግን በዚህ መንፈስ ውስጥ፡ በማይሞተው፡ የዘላለም ሕይወት፡

ምልክቱ በዚያ ያርፋል። እርሱም “በመጨረሻው ቀን እንደገና አስነሳዋለሁ፡” በማለት ቃል ገብቷል።

159 ያው ኢየሱስ ክርስቶስ እዚህ አለ። መልእክተኛው እሱ ነው። እሱ... መልእክቱ **ይኸውና**፡ መልእክቱን የሚለይበት መልእክተኛም እሱ ነው። መልእክተኛው እኔ አይደለሁም። መልክተኛው እሱ ነው፡ መልእክቱም **ይህ** ነው። የመልእክቱ መልእክተኛ እንዴት ሊሆን ይችላል በማለት፡ **ከዚህ** ጋር የማይስማማ መንፈስ ካላችሁ? ምልክቱ ብቻ ነው የሚለየው። ኣሜን።

160 ደስ ደስ አለኝ። በእውነት ደስ አለኝ። አሁን መብረር እንደምችል ይሰማኛል፡ ያመንኩትን አውቃለሁና፡ ህይወቴንም በትንሣኤው ከእርሱ ጋር ሲታወቅ አይቻለሁ። መገኘቱ እዚህ አለ። ተቀበሉት፡ ወዳጆች ሆይ፡ እባካችሁ፡ በልባችሁ ውስጥ አድርጉት።

161 ሁላችንም በመሠዊያው ዙሪያ መጥተን እንደምንጸልይ አውቃለሁ። ያ የድሮ የሜቶዲስት ሀሳብ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲህ አድርገው አያውቁም ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው፡ “ያመኑት ሁሉ ተጠመቁ።” በትክክል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመሠዊያ ጥሪ የሚባል ነገር የለም። ያ እኛ ራሳችን የጨመርነው ነገር ነው፡ ምንም ችግር የለውም። እግዚአብሔር የሚባርከው ማንኛውም ነገር፡ ምንም ችግር የለውም።

162 ለምሳሌ ጨርቆችን ይቀባሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደዚህ ያለ ነገር አልነበረም። “ከጳውሎስ አካል ልብስ እና ቁራጭ ልብስ ይወስዱ ነበር።”

163 ይሁን እንጂ የትም ሆናችሁ፡ ይሄን ማድረግ በፈለጋችሁት መንገድ ብታደርጉት፡ በወንበራችሁ ላይ፡ በመሰዊያው ላይ፡ ምንም ችግር የለውም። ዋናው ነገር፡ ያንን ምልክት፡ በላያችሁ ላይ አድርጉ። ከዚያ በኋላ ራሳችሁን ፈትሹ፡ በህይወታችሁ የሚሆነውን ህይወት መርምሩት፡ ምልክት መደረጉ እና አለመደረጉ እዩት። ካልተደረገ፡ እንግዲያውስ ሽክማችሁን ሁሉ፡ አስወግዱ፡ እና ምልክት እስኪደረግባችሁ ድረስ፡ ተመልሳችሁ ኑ።

164 እንጸልይ። የሰማይ አባት ሆይ፡ ምናልባት በችኮላ ተ—ተ—ተናግሬ ይሆናል፡ ነገር ግን፡ ጌታ ሆይ፡ ሚስማር በደንብ ካልጠበቀ በቀር እንዴት ይይዛል? አባት ሆይ፡ በሰዎች ልብ ውስጥ እንዲጣበቅ፡ እጸልያለሁ፡ ተራ ነገር አለመሆኑን ያዩ ዘንድ ይህ ይሁን። አንዳንድ ድርጅቶችን፡ አንዳንድ ኀሳዎችን እና አንዳንድ የአምልኮ ሥርዓቶች፡ የሆነ ሰው፡ ወይም ራሴን፡ ወይም ሌላ ሰውን፡ እያስተዋወቅኩ አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስን እንጂ። “ሁሉንም ድርጅቶች አንድ ላይ እጥላለሁ፡” ስድስቱም የደርዘን ግማሽ ከአንዷ ናቸው፡ እንደ ቃልህ፡ “ከጋለሞታይቱ አሮጊቷ እናት ናቸው፡” መጽሐፍ ቅዱስ በራዕይ 17 ላይ፡ “የጋለሞታዎች ሁሉ እናት ተብላለች።” ስለዚህ ወንድ ሊሆኑ አይችሉም። ሁሉም ጋለሞታዎች ስለሆኑ፡ ሁሉም ወደ ዓለማዊነት አልጋ ላይ ወጥተዋል። እኛም በጴንጤዎች እና በሌሎች፡ ይህ ሲሆን አይተናል።

165 አንተ ግን፡ ኢየሱስ ሆይ፡ አሁንም ኢየሱስ ነህ። ስለዚህ የክርስቶስ መልእክት፡ ቃሉን እንጂ፡ የቤተ ክርስቲያንን መልእክት አይሰሙ። ጌታ ሆይ፡ ዛሬ፡ ራስህን፡ ከአማኞች ጋር ለይ። የታመሙትን ሁሉ ፈውስ። ኃጢያታችንን ይቅር በለን፡ ጌታ። እ—እጸልያለሁ፡ እንደ አገልጋይህ፡ እባክህ ኃጢአቴን ይቅር በለኝ፡ የዚህን ሕዝብ ኃጢአትም ይቅር በል። አምናለሁ፡ ጌታ ሆይ። ስለ

ህንጻዎቻቸው—ሁሉም ክፍያን ከፍለዋል፡ ምንም ጥርጥር የለውም፡ እና ገንዘባቸውን አውጥተዋል፡ ጌታ ሆይ፡ እነሱ—ያላቸው—ያላቸው ሁሉንም ነገር አድርገዋል። አምላክ ሆይ፡ ማናቸውም ይሄን እንዳይሰቱ እጸልያለሁ፡ ጌታ ሆይ። ለሁሉም ይሁንላቸው!

166 ይ—ይሄን በቅንነት ነው የማደርገው፡ ቢሆንም፡ ጌታ ሆይ፣ አንተም ጠበቅ አርገው። ተግሳጽ ፍቅር እንደሆነ፡ እናውቃለንና። ፍቅር ይገስጻልና። እኔም እጸልያለሁ። ለዛም ነው ህዝብህን የምትገስጻቸው፡ ስለምታፈቅራቸው ነው፡ እያንዳንዱ ኃጢአትም መልስ ሊሰጠው ይገባል።

167 እናም፡ አባት ሆይ፡ እኛ ኃጢአታችንን ስንናዘዝ፡ አሁን ይቅር እንድትለን እጸልያለሁ። ጌታ ሆይ፡ እጅግ ርቀን ተቅበዘበዝን። ጌታሆይ፡ እራሴን ከጴንጤቆስጤ ህዝብ ጋር ለይቻለሁ። እ—እኔም አንዱ ነኝ። እኔም—እግዚአብሔር ሆይ፡ ሁላችንንም ይቅር እንድትለን፡ እጸልያለሁ። እና ከመሪዎች መካከል እንዳንዶቹን ወስደህ መልሳቸው፡ እና—ወደ ቀራኒዮም አንድ ጊዜ ይመልከቱ፡ ከዚያ ቄስ፡ ወይስ ኤጲስ ቆጶስ፡ ወይም ምንም ይሁን ምን መሆን እንዳለባቸው ይረሳሉ፡ በዚህ መንግሥት ውስጥም ታላላቅ እንዳልሆንን ያውቃሉ። ሁላችንም የእግዚአብሔር ልጆች ነንና። አሁን እንድትረዳን እጸልያለሁ። ዛሬ፡ ራስህን በመካከላችን ለይ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጠይቃለን። ኣሜን።

168 አሁን የጸሎቱን መስመር ከመጀመራችን በፊት፡ ከዚህ በፊት እዚህ መጥቶ የማያውቅ ሰው ሊኖር ይችላል። ማን እንደሆናችሁ እኔ አላውቃችሁም፡ እግዚአብሔር ግን ያውቃችኋል። የተናገርኩት ነገር እውነት ከሆነ፡ እውነት መሆኑን እና አለመሆኑን፡ እግዚአብሔር ይለየው፡ ማረጋገጫው ያ ነውና። ከሙታን ከተነሣ፡ ትናንትም፡ ዛሬም፡ ለዘለአለም ያው ነው። በዮሐንስ ወንጌል 14:12 ላይ፡ "ያመነ" ብሏል፡ ሊያምን የሞከረ አላለም። "በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል።" ልክ ው?

169 አንድ ሰው፡ "'የሚበልጥ ታደርጋላችሁ'" ብሏል አለ። ልክ ነው። "አዎን፡ ወንጌልን እንሰብካለንና፡ የሚበልጠውም ይህ ነው፡" አልኩት።

170 እሱ ያደረጋቸውን ነገሮች አድርጉና፡ ያን ጊዜ ይህ ማረጋገጫ ይሆንልኛል፡ አያችሁ፡ ከዚያ በኋላ ስለሚበልጠው ነገር እንነጋገራለን። በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ካደረገው በላይ አሁን እያደረገ ያለውን ታላቅ ነገር ላሳያችሁ እችላለሁ። ይህም፡ ወንጌልን መሰበክ ብቻ አይደለም፥ ይህ በምልክቶች እና በተአምራት ውስጥ ነው። የጊዜ ገደብ የለውም። እመኑ ብቻ። ኢየሱስ ክርስቶስን፡ ከሙታን ያስነሣው፡ እና ከሁለት ሺህ አመታት በኋላ፡ ሕያው መሆኑን ለእኛ ያሳየን፡ የሰማይ አምላክ፡ ይህ መልእክት ትክክል መሆኑን፡ አሁን ይለይ። ምልክቱ መቀባት አለበትና።

171 አሁንም፡ እናንተ ደዊው እና ህመም ያለባችሁ ሁሉ ሆይ፡ ጸልዩ፡ በትህትናም እንዲህ በሉ፦ "ጌታ ሆይ፡ አንተ 'በድካማችን ስሜት ሊነካ የሚችል ሊቀ ካህናት' መሆንህን እምናለሁ። አሁንም አንተ ከእኛ ጋር፡ እንዳለህ፡ ይህ አገልጋይ ነግሮናል፡ እንግዲያውስ አብረኸን ሆነህ እራስህን ከእኛ ጋር እንድትለይ እፈልጋለሁ በሉ።" አሁን፡ ሁላችሁም ጸልዩ።

172 አሁን አንድ ነገር መናገር የእግዚአብሔር ፈንታ ይሆናል። እንዴት ያለ ጊዜ ነው! ኦህ፡ ማይ! እሱ ሲመጣ ምን እንደሚሰማችሁ፡ ማወቅ ብትችሉ እመኛለሁ፡ መላውን ዓለም የእናንተ ነውና። አሜን። ምንም አይነት ሰይጣን ይሁን ምንም ማድረግ አይችልም፡ የተሸነፈ ነውና። የኔ ጌታ ህያው ነው። ሁሉም በእጃችን ነው። አሜን።

እባካችሁ እጅግ ጸጥ በሉ። አትንቀሳቀሱ። አርፋችሁ ተቀመጡ።

173 በተሽከርካሪ ወንበሮች፡ እና በሌሎች ነገሮች ላይ ያላችሁ ሁላችሁ፡ ረዳት የለኝም አትበሉ። እመኑ። በጽሎት መሰመር፡ አ—አልፋችኋል፡ በተደጋጋሚ አልተሳካላችሁም። ያልተሳካለት፡ የጸለየላችሁ አገልጋይ አይደለም። እምነታችሁ ነው፡ ከዚህ በኋላ ምንም ማድረግ አልችልም ብላችኋል። እመኑ ብቻ።

174 ይኸው፡ እዚህ ተቀምጣ ባለች ጥቁር ሴት ላይ፡ ያ ብርሃን መጥቷል፡ እጆችኋን **እንዲህ** አድርጋ በቆመችው ሴት ላይ። አዎን። እየጸለይሽ ነበርሽ። አዎን። የሱ ነብይ፡ ወይም አገልጋዩ እንደሆንኩ ታምኛለሽ? ሰዎችን በጣም ስለሚያደናቅፍ፡ እንዲህ ማለት የለብኝም። ያለሽ አንድ ነገር ነው…

175 እዚህ ጋር ልክ እንደ ጌታችን እና በጉድጓዱ አጠገብ እንደነበረች ሴት፡ አንድ ነጭ ሰውዬ፡ እና አንድ ጥቁር ሴት፡ ሁለታችንም ከተለያዩ ዘሮች ቆመናል። የጎሳ ልዩነት እንደሌለ አሳውቋቸዋል። ቀለሞቻችን በሱ ዘንድ ምንም ግንኙነት የላቸውም። ሁላችንም አንድ ነን… ደም መሰጣጠት እንችላለንና። እግዚአብሔር፡ ዓለምን ሁሉ፡ ከአንድ ደም ፈጠረ።

176 ራስ ምታት አለብሽ፡ ከፍተኛ ራስ ምታት ነው። ሌላ ደግሞ በልብህ ላይ ሽክም አለብሽ፡ ሰለ ልጅሽ ነው። እና… እጅግ ችግር ላይ ወድቋል። [ያቺ እህት "ኣሜን፡" አለች።—አርታዒ።] በትክክል ነው። ልክ ነው? ["ኣሜን።"] በትክክል።

177 ከአጠገብሽ የተቀመጥችው ያች እመቤት፡ ከአንቺ ጋር ትመስላለች፡ እናትሽ ናት። [ያቺ እህት "ኣሜን፡" አለች።—አርታዒ።] በትክክል። ["እግዚአብሔር ይመስገን!"] እሷም የሆነ ችግር ገጥሟታል።

178 ያምኑኛል፡ እመቤት? [እናትዬው "ኣሜን፡" አሉ።—አርታዒ።] ያምናሉ? የእርሶ ችግር የጎን ህመም ነው። በትክክል። ያመሞት ጎኖት ነው። ልክ ነው? ልክ ከሆነ፡ እጆትን ከፍ ያድርጉ። ከእንግዲህ አያሰቸግሮትም። እርሶ ማን እንደሆኑ እግዚአብሔር ከነገረኝ ያምናሉ? ወይዘሮ ሎዌል ኖት። ["ኣሜን።"] ትክክል። ["ኣሜን።"] በጣም ጥሩ፡ ጌታ ኢየሱስ መሻታችሁን ሰጥቷችኋልና፡ በሰላም ሂዱ።

179 እዚያ መጨረሻ ላይ ሌላ ትንሽ ጥቁር ሴት ተቀምጣለች፡ እያየችኝ ነው፡ ውስጧን የ—የሰባበረ ነገር አለ። በቀጥታ እኔን እየተመለከተችኝ ነው። አምናለች። ያም፡ ውስጧ ላይ ያለውን አይታያችሁምን? በኩላሊት ህመም እየተሰቃየች ናት። በትክክል። አሁን አብቅቷል፥ እሱ ፈውሶሻል። አሜን።

180 ለምን አታምኑም? "ካመናችሁ፡ ሁሉም ነገር ይቻላል።" ታምናላችሁን? [ጉባኤው "ኣሜን፡" አለ።—አርታዒ።] ይኸውላችሁ… ጥቁሮችን ተመልከቷቸው! እናንተ ነጮች ሆይ፡ እምነታችሁ ወዴት አለ?

181 አሁንም እዚያ ጋር የተቀመጠችው ጥቁር ሴት ተመልከቷት፡ እያየችኝ ነው፡ ወፍራም ሴት። የጉልበት ህመም አለባት። ሌላ ህመም ደግሞ አለባት፡ የልብ ህመም አላት። አዎን። እና ድክመት፡ መወዛወዝ እና የመሳሰሉት ነገሮች አሏት፡ በተለይ ለመተኛት ስትሞክሪ፡ ትታፈኛለሽ። አየሽ? ትናንት ማታም አጋጥሞሽ ነበር። ይኸውልሽ፡ እኔ አእምሮሽን እያነበብኩ አይደለም፡ የጸለይሽውን ጸሎት አውቃለሁ እንጂ። ዛሬ፡ በዚህ ልትጠሪ ፈልገሻል፡ እነሆ እርሱም መልሶልሻል። አሁን አንቺም መነሳት ያቅትሻል፡ የአርቲራይተስ ችግር አለብሽ። ትክክል ነው። እና፡ ከዚያ ሌላም፡ የሆድ ህመም አለብሽ፡ ይህም በሆድሽ ውስጥ ያደገ ነገር አለ። እውነት ነው። አሁን እኔ የሱ ነብይ እንደሆንኩ ታምኛለሽን? እንዲሁ ማለቴ፡ አይቀርም። እመኚ፡ እና ትፈወሻለሽ።

182 **አንተስ** የሆድ ችግርህ? እግዚአብሔር የሆድህን ችግር፡ በተቀመጥክበት፡ እንደሚፈውስ ታምናለህ? ታምናለህ? በጣም ጥሩ፡ እንግዲያውስ የሆድህን ህመም ፈውስ ይሁንልህ። አሜን።

183 እዚያ ጋር ያለሽው፡ እመቤት፡ ትንባሆን ማጨስ ማቆም ትፈልጊያለሽ? እግዚአብሔር ትንባሆ ማጨስን እንድታቆሚ እንደሚያደርግሽ ታምኛለሽ? ለረጅም ጊዜ ሞክረሻል። የሆድ ችግርም፡ አለብሽ፥ ትንባሆ ለማቆም ሞክረሻል። የሆድሽ ችግር መነሻው ያ ነው። ትተዋቸው ይሆን? እርሱን ለመንካት ባለሽ እምነት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ከአንቺ እነሣሁት።

እግዚአብሔርን እንድታምኑ እጠይቃችኋለሁ!

184 እነሆ አንዲት ምስኪን ሴት ተቀምጣ... በሆስፒታል ውስጥ፡ በካንሰር እየሞተ ላለ ዘመዷ፡ እየጸለየች ናት። ትክክል። አጎቷ ነው። ልክ ነው። አንቺም... የአገልጋይ ሚስት ነሽ። በሙሉ ልብሽ እመኚ፡ ሰውዬው ይፈወሳል።

185 እግዚአብሔርን እንድታምኑ እጠይቃችኋለሁ! ይህ ምንድን ነው? የኢየሱስ ክርስቶስ መለያ ነው። "ክርስቶስ ምንድን ነው፡" ብላችኋል?

186 እርሱ ቃል ነው። "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ቃልም ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ።" "ቃሉ ሁለት-አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ የተሳለ ነው፡ የልብንም አሳብና ስሜት የሚያውቅ ነው።" በመጨረሻው ዘመን ቃሉ በመካከላችን እንደመጣ አታዩምን? የእግዚአብሔርን ቃል ወስዶ ኢየሱስ ክርስቶስን እያስተዋወቀ ያለው መንፈስ ቅዱስ ነው፡ እርሱም ምልክት ነው። ኣሜን። ታምናላችሁ? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—እርታዒ።]

187 የጸሎት ካርዶች የያዛችሁ ሰንቶች ናችሁ? የጸሎት ካርዶች ያላችሁ ሁሉ **በዚህ** መሰመር፡ **በዚህ** መሰመር ቁሙ። ቁሙ፡ ሁላችሁም በዚያ በኩል፡ ያኛው ወገን እዚህ በመተላለፊያው ውስጥ ቁሙ። አይደልም፡ እባካችሁ፡ እዚያ ጋር፡ በቀኝ-በኩል ባለው መተላለፊያ። አስተናጋጆች፡ በሰፍራችሁ ሁኑ። እነሱ ሲጨርሱ፡ ሌሎች ይነሱ፡ እነሱም ከጨረሱ በኋላ፡ ሌላኛው ወገን ደግሞ ይቀየራሉ። አሁን ሁሉም ሰው በትህትና ይሁን።

188 መንፈስ ቅዱስ ስብሰባውን ይረከብ፡ ይሄን ለማረጋገጥ በቂ ነገር ተብሏል ተደርጓልምና። እሱ እዚህ እንዳለ ስንቶች ታምናላችሁ? እሱ ምልክት እንደሆነ ስንቶች ታምናላችሁ? ቃሉ እንደሆነ ስንቶች ታምናላችሁ? [ጉባኤው መደሰት ጀመረ—እርታዒ።] ይኸውላችሁ፡ የዕብራውያን መጽሐፍ ይህ እንደተናገረ ስንቶች ታውቃላልችሁ፡ ማለት፡ "የእግዚአብሔር ቃል በልብ ውስጥ ያለውን

ሐሳብ እንደሚያውቅ”? ስንቶች ታውቃላችሁ? ኢየሱስ እርሱ ቃል ስለሆነ በልባቸው ውስጥ ያለውን ሐሳብ ሊያውቅ የቻለበት ምክንያት፡ ለዚህ እንደሆነ ስንቶች ታውቃላችሁ? ስንቶች ታምናላችሁ? በነቢያት ዘንድ የነበረውም ይህ እንደሆነ ስንቶች ታውቃላችሁ? እነርሱም ቃሉ የመጣላቸው ናቸው። አሁንስ ቃሉ ወደ እኛ ቢመጣ፡ ያው አይሆንምን? ታዲያ ቃሉን ይታወቅ ዘንድ የሚለየው ቃል፡ እንዴት በቃሉ ይሳሳታል? አቤት፡ ማረን! ትህትና!

189 ይኸውልሽ፡ እዚያ ጋር የተቀመጠችው እመቤት፡ እሷም፡ የልብ ህመም አለባት። በአጋጣሚ ዞር ስል ነካኋት። ወይዘሮ ግራንት አይደለሽምን? ይህን ፈጽሞ አላውቅም። ይሁን እንጂ አንቺ ወይዘሮ ግራንት ነሽ፡ ምክንያቱም በዚያ ሁኔታ አይቼሻለሁ። የሚያስቸግርሽ የጭንቀት ችግር አለብሽ። ልጅሽም፡ ሌላ ነገር አለበት... ደሙ፡ ነው፡ ይንጠባጠባል። እንድታምኑ እጠይቃችኋለሁ! ኣሜን። የሁኔታው ባለቤት እሱ ነው። የሞት አለቃ እርሱ ነው።

እንጸልይ።

190 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ እዚህ ህንጻ ውስጥ፡ ህልውናህ ሲቀባን፡ ይህ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ እናውቃለን፡ ጌታ ሆይ፡ እነዚህ መኃረቦች የነካ ሰው ሁሉ ይፈወስ ዘንድ፡ እጸልያለሁ።

191 በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተማርነው፡ በአንድ ወቅት፡ ህዝብህ፡ በጉዞ ላይ በነበሩ ጊዜ፡ ቀይ ባህርን እያቋረጡ ነበር፡ ወደ ተስፋይቱ ምድር በመንገድ ላይ ሳሉ፡ ባሕሩ ተጋረጠባቸው። እግዚአብሔርም በዚያ በእሳት ዓምድ ሆኖ፡ በቁጣው አይኖቹ ተመለከተው፡ ባሕሩም ፈርቶ፡ ወደ ኋላው ሸሸ፡ እስራኤልም በጉዞ መስመር፡ ወደ ተስፋይቱ ምድር ሄደ።

192 አቤቱ አምላክ ሆይ፡ ዓይኖችህ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም በኩል፡ ዛሬ በእጃችን በያዝናቸው በእነዚህ የመሃረብ ምልክት ይመልከቱ። እነዚህ በነካ ሰው ሁሉ ላይም፡ ህመም ሁሉ ይፍራ፡ ወደ ኋላ ይሸሽ እና ሰዎችም ወደ ጥሩ ጤና ቃል ኪዳን ይሻገሩ። “የእምነት ጸሎት ድውያንን ያድናል።” በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እንዲህ ይሁን። ኣሜን።

193 ስንት አማኝ የሜቶዲስት ሰባኪዎች፡ የባፕቲስት ሰባኪዎች፡ የፕሪስባይቴሪያን ሰባኪዎች፡ የባፕቲስት ሰባኪዎች፡ ሉተራን፡ ወይስ ጴንጤቆስጤዎች አላችሁ? ስንቶቻችሁ ይህ እውነት ነው ብላችሁ ታምናላችሁ? እንግዲያውስ ስለበሽተኞቹ ስንጸልይ ሳለን ኑና እዚህ ቁሙ። እናንተ ያመናችሁ ሰባኪዎች ሁሉ፡ ወደዚህ ውጡ።

194 ችግር የለውም፡ አይደል? ወንድም ግራንት፡ ችግር የለም? [ወንድም ግራንት “አዎን፡” አለ።—አርታዒ።] ኸሃ-ሃህ።

195 ወደዚህ ና፡ ወንድሜ። ወንድም ግራንት ለታመሙ የመጸልይ አገልግሎት አለው። ጀግና ሰው፡ ጥሩ ሰው፡ እግዚአብሔር የሚሰማው እና ጸሎትን የሚመልስለት ሰው፡ ወንድም ግራንት። ዛሬ ክንዶቼን በእሱ ላይ ጣል አድርጌ፡ ወንድሜ ስለው ደስ ይለኛል። አሁን እዚህ ወርዶ ከእኔ ጋር ይጸልያል።

196 በዚህ መስመር ስትመጡ፡ ልክ ከመስቀል ስር እንደምትመጡ። ወንድሞች፡ እዚሁ፡ እዚሁ ድርብ መስመር ስሩ። ድርብ መስመር ስሩ፥ አንዳንዶች ወደዚህ፡ አንዳንዶቹ ወደ ታች።

197 ወንድም ሮይ ቦርደርስ፡ የት ነህ? ወንድም ሮይ ቦርደርስ፡ እዚህ ያለ መስሎኝ ነበር። [አንድ ሰው "አሁን ይመለሣል፡" አለ።—አርታዒ።]

198 ተመልከቷቸው፡ እነዚህ አገልጋዮች፡ እሺ! እዩአቸው። ወንድሞች ሆይ፡ እጅግ ደስ ያሰኘኛል። የመስቀሉ አገልጋዮች፡ ከመልእክቱ ጋር ራሳቸውን ለመለየት እዚህ የቆሙ ሰዎች። ምን ሊሆን ይችላል?

199 አሁን፡ ተመልከቱ፡ በአገልጋዮች ላይ አታድርጉት። ራሳቸውን ለመለየት መጥተዋልና። በዚህ በኩል ሰታልፉ፡ ምልክቱን-... በፊታችሁ ያዙና፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ እኔ ኃጢአቴን ተናዝዝሁ። በምላሹ፡ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ሰጥተኸኛል። እኔ የተገዛሁ ንብረት ነኝ። ከዛሬ ጀምሮ፡ ኃጢአት ሕመም ወይም ምንም ነገር ሊይዘኝ አይችልም። በትክክል እየተንቀሳቀስኩ ነው።" ኦህ፡ ይህን በፊታችሁ፡ በደንብ ያዙና፡ በዚህ በኩል እለፉ፡ እግዚአብሄርም ይፈውሳችኋል በኃሴት፡ በደስታ፡ ደህና ሆናችሁ ትወጣላችሁ። ታምናላችሁ? [ጉባኤው "ኣሜን፡" አለ።—አርታዒ።]

200 አሁን እዚህ ያለን ሁላችንም፡ ወንድሞች፡ አብረን እንዳለን፡ አንገታችንን ዝቅ እናደርጋለን። ምን እንደሚሆን አናውቅም። እኛ አናውቅም። ዛሬ ከሰአት በኋላ ማንም የታመመ ሰው ከሕንፃ የሚወጣበት ምንም ምክንያት የለም። ያንን ምልክት በልባችሁ ያዙ፡ በዚህ የጸሎት መሰመር እለፉ፡ ህይወታቸውን ለዚህ አ—አገልግሎት የለዩ፡ አገልጋዮች፡ እዚህ ጋር ይቆማሉ፡ እናንተ በምታልፉበት ጊዜ እጆቻቸውን በእናንተ ላይ ይጭናሉ።

"ወንድም ብራንሃም፡ ለምን እንዲህ አደረግክ፡" ብትሉኝ?

201 ሁሉም ሰው፡ ይህን እንዲያውቅ፡ እፈልጋለሁ... እኔ ፈዋሽ አይደለሁም። ይህ ሰው እንደማንኛውም ሰው ለታመሙ የመጸለይ መብት አለው። እውነቱን ለመናገር፡ እግዚአብሔር ጸሎቴን ከመመለሱ በፊት እንደሚመልስላቸው አምናለሁ። እኔ ደክሞኛል፡ ዝያለሁ ወዘተረፈ። ጸሎታቸውን እንደሚመልስ አ—አምናለሁ። እና እዚህ እራሳቸውን ለመለየት፡ በመካከላቸው ቆመዋል። ቦታቸውን ለመተካት አላፈሩም። እንደዚህ አይነት ሰውን አደንቃለሁ።

202 አሁን፡ ወንድሞች ሆይ፡ ሰሜታችሁን እውቃለሁ። እኔም፡ ከእናንተ ጋር አንድ ነኝ። እዚህ ቴክሳስ ውስጥ፡ መረቤን ከእናንተ ጋር የሰራሁ ሰው ነኝ፡ እግዚአብሔር፡ ለሕይወት የወሰነውን ዓሣ እያንዳንዳቸውን እዚያው ለመያዝ እሞክራለሁ። የተቻለኝን እያደረግኩ ነው። እኔም መቶ በመቶ፡ ከእናንተ ጋር ነኝ። አንዳንድ ጊዜ ሰለ ድርጅት እና ነገሮች እጅግ እጮኻለሁ። ወንድሜ ሆይ፡ ይህ ማለት እናንተን እቃወማለሁ ማለት አይደለም። አንዳንድ ሃይማኖታዊ አሰተምህሮዎች ምክንያት፡ ማለት ወንድማማች ከመሆን የሚለየንን ሰርዓት እቃወማለሁ። በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ወንድማማቾች ነን። ተመሳሳይ ምልክት ይዘናል። አንድ አይነት ደም ተቀብለናል፡ ሰለዚህ ያንን እንመን። ወንድሞች ሆይ፡ እያንዳንዳችን፡ ከዚያ ደም በታች መገናኘት እንችላለን (አንችልም ወይ? )።

203 ለምሳሌ፡ እኔ የተሾምኩት እንደ የባፕቲሰት አገልጋይ ነበር። ምናልባት ሜቶዲሰት፡ ወይም ሉተራን፡ ወይም ፕሪቢሰተሪያን፡ ጴንጤቆሰጤ፡ አሃዳውያን፡ ሁለታውያን፡ ሥላሴአዊያን፡ ወይም ሌላ ነገር፡ ቸርች ኦፍ ጋድ፡ ሌላ ነገር ልትሆኑ

ትችላላችሁ። ያ ምንም ለውጥ አያመጣም። በጥቃቅን ነገሮች መስማማት ካቃተን፡ እሱን እንተወው።

204 መስማማት በምንችልባቸው ነገሮች ላይ እናተኩር፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞቷል፡ እንደገናም ተነሣ ምልክትም ሰጠን። በዚህ መስመር የሚያልፉትን እነዚህን የታመሙ ወንድሞችን እና እህቶችን ለመንካት፡ ከጸሎታችን ጋር እዚህ ቆመናል። በሙሉ ልቤ አምናለሁ።

205 የሆነ ነገር ሲከሰት እይቻለሁ። ኣሜን። እብድ እንደሆንኩ እንደምታስብ አውቃለሁ፡ ነገር ግን ጥሩ እብድነት እየተሰማኝ ነው። እንዲህ ሆኜ መቆየት እንደምችል ተሰፋ አደርጋለሁ። አዎን፡ ወዳጄ። በቃ ጥሩ ስሜት ይሰማኛል።

እንጸልይ።

206 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ እኔ ከእነዚህ ወንድሞች ጋር እንደሆንኩ ራሴን ለመለየት፡ ከዚህ መድረክ ላይ፡ ወደ ታች እየሄድኩ ነው። ሁላችንም ምልክቶቻችንን፡ በእጃችን እና በልባችን ውስጥ እንደያዝን፡ ራሴን ከነሱ ጋር መሆኔን እለያለሁ። “እጆቻቸውን በድውዮች ላይ ይጫናሉ፡ እነሱም ይፈወሳሉ፡” የሚለውን ትእዛዝህን እንደታዘዝን። በዚህ የሚያልፉ ሰዎች ሁሉ፡ መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበሉ፡ በሙሉ ልባቸው እንዳመኑ፡ ዳግም-የተወለዱ የእግዚአብሄር ልጆች እንደሆኑ፡ ምልክታቸውን ያቅርቡ። ሲያልፉም፡ ያንን በሽታና የአካላቸውን ስቃይ ይገሰጹት። እናም እምነታቸው እንዳዳናቸው አውቀው፡ በደስታ ከዚህ ይውጡ።

207 አሁንም፡ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡ በብሉይ ኪዳን፡ ከመስዋዕታችን አንድ መሆናችንን ለመለየት፡ እጆቻችንን፡ በመስዋዕቱ ላይ እንደምንጭን፡ አሁንም እጃችንን በኢየሱስ ላይ ጭነን ራሳችንን ከሱ ጋር መሆናችንን እንለያለን። እሱም በምልክትና በድንቅ፡ ማንነቱን ከእኛ ጋር መሆኑ በመለየት፡ እጆቹን በእኛ ላይ ጭኗል። እናም እጃችንን በበሽተኞች ላይ እየጫንን፡ ራሳችንን ከነሱ ጋር ለመለየት፡ እምነታችን ከእነሱ ጋር የተያያዘ ነው። ሕመም መወገድ አለበት፡ ይሄን ለመቀበል ወደዚህ ስንሄድ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ያድርግልን።

ምእመናን ሁሉ ይጸልዩ።

208 ሮይ ወይም የሆነ ሰው እዚህ መጥታችሁ በዚህ ማይክሮፎን ቁሙ፡ እና መስመሮቹን ቀጥ አስተካክሉ።

209 ይኸውላችሁ፡ አሁን በዚህ ስታልፍ፡ እያመናችሁ፡ በጸሎት ኑ። በታመሙ ሰዎች ላይ እጃችንን እንጭናለንና። በቀጥታ ኑ። ጸልዩ። በእነዚህ አገልጋዮች መስመር ውስጥ ስታልፍ፡ በክራንች ላይ የምትሄድ ከሆነ፡ ጣሏቸውና ተራመዱ። ካንሰር፡ እና ህመም ያላችሁ ከሆነ፡ እንዲህ በሉ፡ “ሐኪሙ ማድረግ የሚችለውን ሁሉ አድርጓል፡ የሚቻለውን ሁሉ አድርጓል፡ ትሞታለህ ብሎኛል። እኔ ግን አልሞትም። ጌታ ሆይ፡ ምልክቴ ይህ ነው። ሰልሳ እና አስር ቃል ገብተህልኛል። እኔም በዚህ አልፋለሁ፡ ይሄን አድርጋለሁ።” አያችሁ፡ ይሄን አድርጉ። ማድረግ ትፈልጋላችሁ? [ጉባኤ “አሜን፡” አለ።—አርታዒ።] በኢየሱስ ስም፡ ይሁንላችሁ። አሜን።

210 በጣም ጥሩ፡ መስመሩ ይለፍ። [ወንድም ብራንሃም እና አገልጋዮች ለታመሙ ሰዎች ጸለዩ፡ አንድ ወንድም **እመን ብቻ** እና ሌሎች መዝሙሮችን

በመዘመር ጉባኤውን እየመራ ነው። በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]

እምናለሁ!
ጥርጣሬዎቼ በሙሉ ምንጭ ውስጥ ተቀብረዋል።

211 ታምናላችሁ? [ጉባኤ "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] አሜን። ኦህ፡ እሱ ድንቅ አይደለምን? ["አሜን።"] አንዳንዶቹ ከአልጋ እና ከስትሬቸር፡ ወዲያው ተነስተው እየሄዱ ናቸው፥ እዚያው ጥለው፡ ተነስተው እየሄዱ ናቸው። ኦህ፣ አሁን የሚያምን ሁሉ፡ ሁሉም ሰው ሊፈወስ ይችላል። ታምናላችሁ? ["አሜን።"]

212 እሰኪ ኮርድ ሰጪን፡ እሺ፡ እህቴ፡ **እወደዋለሁ**፡ የሚለውን የጥንት መዝሙር፡ "እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ ሰለወደደኝ..."? ሁላችንም ድምጻችንን፡ እና እጆቻችንን፡ ልባችንን፡ ወደ እግዚአብሔር ከፍ እናድርግ፡ እና እንዘምር፡ "እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ፡ ሰለወደደኝ።" ሁሉም ሰው አሁን።

እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ
ሰለወደደኝ
መዳኔንም ገዛሁ
በቀራንዮ...

213 አንዲት ሴት፡ ከዊልቸር ወንበሩ ላይ ተነሰታ፡ በሁለት ሰው ድጋፍ በዚህ በኩል እየተራመደች ናት። "እ... " እጆቻችንን ወደ እግዚአብሔር እናወዛውዝ፡ "እወደዋለሁ!"

እወደዋለሁ
ሰለወደደኝ
መዳኔንም ገዛሁ
በቀራንዮ...

አሁን፡ ሁላችሁም እናወድሰው!

214 ክብር ለእግዚአብሔር! ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ሰለ ቸርነትህ፡ ሰለ መገኘትህ፡ እንዴት እናመሰግንሃለን። አቤቱ፡ ጌታ ሆይ፡ ሰለ ምልክት እናመሰግንሃለን። ድነናል እናም በመንፈስ ተሞልተናል፡ መንፈስ ቅዱስ አሁን በሰውነታችን ላይ ሰፍኗል። አባት ሆይ፡ ለዚህ እጅግ እናመሰግናለን! ኦህ፡ በኢየሱስ ሰም እናመሰግንሃለን። ኣሜን። ኣሜን።

215 ሁሉም ሰው ተጨባበጡ፡ "ጌታ ይመስገን!" ተባባሉ፡ እርሰ በርሳችሁ ተጨባበጡና፡ እንዲህ ተባባሉ፡ "ጌታ ይመስገን! ጌታ ይመስገን!" (... ? ... ) በጣም ጥሩ፡ አሁን፡ ሁላችሁም አንድ ላይ፥

እወደዋለሁ፡

እጅ ወደ ላይ፡ ልቦች ወደ ላይ።

እ...

ከልባችሁ ብቻ ግለፁት።

ሰለወደደኝ (ታሰናብትልናለህ? )
መዳኔንም ገዛሁ
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

216 አሁን በትህትና አንገታችንን ዝቅ እናደርጋለን፡ አሁን አገልግሎቱን ለማሰናበት ለወንድም ግራንት ልሰጠው፥ እያንዳንዳችሁን አመሰግናለሁ። በመጀመሪያ፡ ጌታን ስለ ቸርነቱ ስለ ምሕረቱ፡ እና በልባችሁ ውስጥ ስለ ተውነው ተስፋ፡ ብቻችን ስለ አለመሆናችንን፡ ስለሚያደርገው ማረጋገጫ አመስግነዋለሁ። ታላቁ አለቃ ካፒቴን በመካከላችን አለ። የንጉሱ ጩኸት በሰፈሩ ውስጥ ተሰምቷል። ታላቅ ኃይሉን እና ምሕረቱን በማየታችን፡ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። እና አሁንም በትህትና አንገታችንን ዝቅ እናድርግ። ወንድም ግራንት።

64-0308 ምልክት
ሶልሰ ሃርቦር ቴምፕል
ዳላሰ, ቴክሳሰ ዩ.ኤሰ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ:

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org